2023

# 2024

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተማሪ

# የስነምግባር ኮድ

www.montgomeryschoolsmd.org

የፌዴራል እና የስቴት ሕጎች፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ፖሊሲ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) አስተዳደራዊ ደንቦች እና ሌሎች መመሪያዎች ሊለወጡና እና በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ያሉትን መግለጫዎች እና ማጣቀሻዎች ሊተኩ ይችላሉ።

ስም ______________________________

አድራሻ ______________________________

ስልክ ______________________________

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

VISION

## ራእይ

ለእያንዳንዱና ለማንኛውም ተማሪ እጅግ የላቀውን ህዝባዊ ትምህርት በማቅረብ መማርን እናበረታታለን።

## ተልእኮ

እያንዳንዱ ተማሪ በኮሌጅ እና በሥራ መስክ ውጤታማ እንዲሆን/እንድትሆን፣ በአካደሚክስ፣ ችግር የመፍታት ዘዴ/ ብልሃት ፈጠራ፣ እና የማህበራዊ ስሜት ክህሎቶች ይኖሩታል/ ይኖሯታል።

## ዋና ዓላማ

ሁሉንም ተማሪዎች የወደፊት ህይወታቸው እንዲዳብር/ እንዲበለጽግ ማዘጋጀት፡ ፡

## ዋነኛ እሴቶች

መማር/እውቀት
ግንኙነቶች
አክብሮት
ልቀት
ፍትኃዊነት/ሚዛናዊነት


Board of Education የትምህርት ቦርድ

Ms. Karla Silvestre ሚ/ስ ካርላ ሲልቨስትሪ
Presidentፕ ሬዚደንት

Mrs. Shebra L. Evans ወ/ሮ ሸብራ ኤል. ኢቫንስ
Vice President ም/ፕሬዚደንት

Ms. Lynne Harris ሚ/ስ ለይኔ ሃሪስ

Ms. Grace Rivera-Oven ሚ/ስ ግሬስ ሪቬራ-ኦቨን

Mrs. Rebecca K. Smondrowski ወ/ሮ ርብቃ ኬ. ስሞንድሮውስኪ

Ms. Brenda Wolff ሚ/ስ ብረንዳ ዎልፍ

Ms. Julie Yang ሚ/ስ ጁሊ ያንግ

Mr. Sami Saheed አቶ ሳሚ ሰዒድ
Student Member ተማሪ አባል

Montgomery County Public Schools (MCPS)
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ
Administration አስተዳደር

Monifa B. McKnight, Ed.D. ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
Superintendent of Schools የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

Mr. M. Brian Hull ሚ/ር ኤም ብራያን ሃል
Chief Operating Officer ዋና ሥራ አስኪያጅ

Patrick K. Murphy, Ed.D. ፓትሪክ ኬ.መርፌ ዶ/ር
Deputy Superintendent ምክትል ሱፐርኢንተንደንት

Mr. Brian S. Stockton ሚስተር ብሪያን ኤስ ስቶክተን
Chief of Staff ዋና የሠራተኞች ሃላፊ

Mrs. Stephanie P. Williams ወይዘሮ ስቴፋኒ ፒ. ዊሊያምስ
General Counsel ጀነራል ካውንስል

Ms. Elba M. Garcia ሚስ ኤልባ ኤም ጋርሺያ
Senior Community Advisor የማህበረሰብ ከፍተኛ አማካሪ

Dr. Patricia E. Kapunan ዶክተር ፓትሪሺያ ኢ ካፑናን
School System Medical Officer የትምህርት ቤቶች የጤና መኮንን



850 Hungerford Drive
Rockville, Maryland 20850
www.montgomeryschoolsmd.org

# 2023–2024

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ተማሪ

# የስነምግባር ኮድ

www.montgomeryschoolsmd.org

ይህ የተማሪ ስነምግባር ኮድ በእንግሊዝኛ፥ በስፓንሽኛ፥ በፈረንሳይኛ፥ በቻይንኛ፥ በኮርያንኛ፥ በቬትናምኛ፥ በአማርኛ፥ እና በፖርቹጋልኛ በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፦ www.montgomeryschoolsmd.org/students/rights/

የተማሪ ስነምግባር ኮድ (አማርኛ)

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

© ሴፕቴምበር 2023
Montgomery County Public Schools
Rockville, Maryland

Maryland's Largest School District
**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**
*Expanding Opportunity and Unleashing Potential*

**OFFICE OF THE SUPERINTENDENT OF SCHOOLS**

ሴፕቴምበር 2023

ውድ ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ እና የሥራ ባልደረቦች

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተማሪዎች የስነምግባር መመሪያ 2023–2024 እትም ሳቀርብላችሁ ደስታ ይሰማኛል። ይህ አስፈላጊ ሰነድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ የስነምግባር ማስተካከያ መርህን በመተግበር ረገድ በቦርድ ፖሊሲ JGA ላይ የተገለፀውን የባህሪ ማስተካከያ፣ የሠላም እና ደህንነት እቅድ ለተማሪዎቻችን ያለንን የማያወላውል ቁርጠኝነት ያሳያል። በዚህ የባህሪ ማስተካከያ መርህ ዋናው ትኩረት ማገገሚያ፣ ተኃድሶ፣ ትምህርት ሰጪ፣ እና በፍትሃዊነት የሚከናወን መሆን አለበት የሚለው እምነት ነው። በተጨማሪም፣ ወረርሽኙን ተከትሎ ተማሪዎቻችን እና ቤተሰቦቻችን የሚያጋጥሟቸውን ልዩ ተግዳሮቶች እንረዳለን። ስለዚህ የሕጎችን አተገባበር በእኩልነት፣ በባህላዊ ግንዛቤ እና የተማሪዎቻችንን ስሜት፣ ችግርና፣ ልምድ የመሳሰሉትን በጥልቀት እያገናዘብን እንተገብራለን። የእኛ ቁርጠኝነት ሁኔታዎችን በማገናዘብ እንደሁኔታው ማስተካከል፣ ማመቻቸት እና ለተማሪዎቻችን ድጋፍ ቅድሚያ መስጠት፣ አስፈላጊ ግብዓቶችን መስጠት እና የህይወት ልምዳቸውን ለመረዳት መጣር ነው።

ለተማሪዎቻችን በምናደርገው የማይናወጥ ቁርጠኝነት፣ ለሚከተሉት ለመሥራት ቃል የገባናቸው ነገሮች ቅድሚያ እንሰጣለን፡ በማህበረሰባችን ውስጥ መተማመንን መፍጠር፣ የአዕምሮ ጤና እና ደህንነት ግብአቶች/ሪሶርሶች ተደራሽነትን ማረጋገጥ እና ለእያንዳንዱ ተማሪ ፍትሃዊ ትምህርትን ማጎልበት። ይህ ሰነድ እና በተማሪዎቻችን የመጀመሪያ አቀራረብ ላይ የተመሰረቱት መርሆዎች ተማሪዎቻችን ከMCPS ጋር በሚያደርጉት የትምህርት ጉዞ ላይ የሚያስፈልጋቸውን ጽኑ ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ ያለንን ቁርጠኝነት ማረጋገጥ አለባቸው።

በቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ማስተካከያ፣ ሠላም እና ደህንነት እቅድ ላይ እንደተገለጸው MCPS ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድን ራዕይ ለማስፈጸም በቁርጠኝነት ይቀጥላል። ይህ ራዕይ በሰራተኞች እና በተማሪዎች መካከል የአዕምሮ እድገትን፣ ስነ ዜግነትን፣ ሃላፊነትን እና መከባበርን የሚያበረታቱ አወንታዊ፣ የመከባበር፣ ስርአት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የተማሪ ማህበረሰብ መፍጠርን ያካትታል። ብዙሃን የትምህርት ቤት ማህበረሰባችን አባላት እያንዳንዳቸው የሁሉንም ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞችን ክብር በመጠበቅ፣ ለመማር ምቹ የሆነ አካባቢን የማዳበር ሃላፊነት እንደሚጋሩ በፅኑ እናምናለን።

ከመልካም ወዳጅነት ጋር

Monifa B. McKnight, Ed.D.
Superintendent of Schools
ሞኒፋ ቢ. ማክኒት ዶ/ር
የት/ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት

………..

# ይዘት

ፈጣን የማጣቀሻ መመሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . i

መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

MCPS ሥነሥርዓት የማክበር መርህ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

የተማሪ ስነምግባር. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

MCPS የሰራተኞች ሀላፊነቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 1

የወላጅ/አሳዳጊ እና የማህበረሰብ ሃላፊነቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 2

ዘላቂነት ያለው ተግባር፣ ቀጣይነት ያለው ፍትሕ፣ እና በዘላቂነት ጠጋኝና ጠንካራ ትምህርት ቤቶች. . . . . 2

የቅደምተከተል/ስነስርአታዊ መስፈርቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

የተማሪ የስነምግባር ህግ አፈጻፀም/አተገባበር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

በዲስፕሊን እርምጃ ላይ ተፅእኖ የሚያደርጉ እሳቤዎች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

የዲስፕሊን ግብረመልሶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 3

ቀጣይነት ያለው ትምህርት የማግኘት መብቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

ወቅታዊ ሁነቶች ጋር የተያያዙ የተራዘሙ እገዳዎችና ስንብቶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

የአካል ጉዳተኝነት ያለባቸው ተማሪዎች እገዳና ስንብት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 4

የባህሪ ማስተካከያዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 5

የግብረመልስ ደረጃዎች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 8

የባህሪ ማስተካከያ ማትሪክስ (Behavior Intervention Matrix) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 10

ስለ ተማሪ ዲሲፕሊን በተመለከተ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና MCPS ደንቦች . . . . . . . . . . . . . 21

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ. . . . . . . . . . . . . . . . በስተጀርባ ሽፋን

# ፈጣን መረጃ ለማግኘት የሚጠቅም መመሪያ
# የተማሪዎች መገልገያዎች/ሪሶርሶች

## የሞንትጎመሪ ካውንቲ ለድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመሮች
**24-ሰዓት መረጃ፣ ወደሚመለከተው ማስተላለፍ እና ጠቃሚ ውይይት**

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማዕከል ለአስቸኳይ ጥሪ ክፍት የስልክ መስመር፡ Hotline/EveryMind/ . . . . . . . 301-738-2255 እና https://www.every-mind.org/
በይነመረብ ላይ የሚያነጋግሩ ሰዎች ያሉበት እና የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፥ 24 ሰዓት የማወያየት አገልግሎት ይሰጣል።

Montgomery County Crisis Center - 240-777-4000
ሞንትጎመሪ ካውንቲ ቀውስ ማእከል
ቀውስ ማዕከል የአእምሮ ጤና ችግር ላጋጠማቸው ግለሰቦች 24/7 ነፃ የድጋፍ አገልግሎት ይሰጣል።

Youth Crisis Hotline of Montgomery County 301-738-9697
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ወጣቶች የድንገተኛ ጥሪ ስልክ መስመር
በሰለጠኑ ካውንስለሮች አማካይነት 24 ሰዓት በስልክ የማማከር ድጋፍ እና ሪፈራል የምስጢር አገልግሎት ይሰጣል።

## የደህንነትና የፀጥታ አስጊ ሁኔታዎችን ሪፖርት ለማድረግ፡-

MCPS ስርአት አቀፍ የድንገተኛ አደጋ አስተዳደር ቢሮ: 240-740-3066
MCPS Office of Systemwide Emergency Management
የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶችን እና ጽ/ቤቶችን ደህንነት የማረጋገጥ ኃላፊነት ያለው ቢሮ።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የተማሪ ደህንነት እና ህግ ማክበር፡- SWC@mcpsmd.org or TitleIX@mcpsmd.org . . . 240-740-3215
MCPS ዲስትሪክት አቀፍ Title IX አስተባባሪ እና ዲስትሪክት አቀፍ የሕፃናት በደል እና ቸልተኝነት ግንኙነት። ስለ ተማሪ ደህንነት እና ደንብ ማክበር (SWC) በዚህ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛል፡- https://www.montgomeryschoolsmd.org/compliance/. SWC ከትምህርት ቤቶች፣ ከጀነራል ካውንስል ጽ/ቤት እና ከሌሎች MCPS ጽ/ቤቶች እና ከማህበረሰብ ኤጀንሲዎች ጋር በመተባበር ፖሊሲዎች፣ ደንቦች፣ እና መመሪያዎች፣ ከሰዎች ግንኙነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን ከመተግበር አኳያ፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ (Title IX ወሲባዊ ትንኮሳን ጨምሮ)፣ እና ማስፈራራት፣ የሕፃናትን በደል እና ቸልተኝነት መገንዘብ እና ሪፖርት ማድረግ፣ ጥላቻና-አድሏዊነት፣ የጥላቻ እና የተማሪ የጾታ ማንነት ጉዳዮችን በሚመለከት ከላይ ከተጠቀሱት መሥሪያ ቤቶች ጋር በመተባበር ይሠራል።

MCPS Cyber Safety dropbox፡- . .CyberSafety@mcpsmd.org
MCPS ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ኦንላይን እንቅስቃሴን ሪፖርት ማድረጊያ Dropbox።

ከኮምፒተር ኔተዎርኮች ጋር ስለተገናኙ ጉዳዮች የጥቆማ መስመር - Cyber Tipline . . . . . . . . . . . . . . . 1-800-843-5678
24/7 ልጆችን ለወሲብ ድርጊት በማባበል የተጠረጠሩትን ሪፖርት ለማድረግ የድንገተኛ ጥሪ የስልክ መስመር፣ ከቤተሰቦቻቸው ውጪ የሚፈፀሙ ወሲባዊ ድርጊቶች፣የህፃናት ፖርኖግራፊ፣የህፃናት ወሲባዊ ቱሪዝም፣የህፃናት የወሲብ ንግድ፣ለልጆች የሚላኩ ያልተጠየቁ ጸያፍ ቁሶች፣የተሳሳተ/የተጭበረበሩ የተጠቃሚ ስሞች እና አሳሳች ቃላትን ወይም በኢንተርኔት ላይ የሚለጠፉ ዲጂታል ምስሎችን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 የሚያገለግል የስልክ መስመር።

Safe Schools Maryland Hotline . . . . . . .833-MD-B-Safe (833-632-7233)
ደህንነታቸው የተጠበቀ የሜሪላንድ ት/ቤቶች የአስቸኳይ ጊዜ ጥሪ የስልክ መስመር
24/7 ስም ሳይገለጽ ነፃ የሪፖርት ማድረጊያ ስርዓት ለተማሪዎች፣ ለአስተማሪዎች፣ ለት/ቤት ሰራተኞች፣ ለወላጆች እና ለጠቅላላው ማህበረሰብ የአእምሮ ጤና ጉዳዮችን ጨምሮ ማንኛውንም የት/ቤት ወይም የተማሪ ደህንነት ስጋቶችን ሪፖርት ለማድረግ ያገለግላል። ስልክ የሚደውለውን ሰው ማንነት በመደበቅ ስለተፈጠረው ክስተት በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አግባብ ካላቸው ቢሮዎች ጋር መረጃ ይጋራል።

Montgomery County Child Protective Services, Department of Health and Human Services
የሞንትጎመሪ ካውንቲ የሕፃናት ጥበቃ አገልግሎት፣ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎት ዲፓርትመንት
(24 ሠዓት ክፍት የስልክ መስመሮች) . 240-777-4417 ወይም 240-777-4815 TTY
ተጠርጣሪ የልጅ ጥቃትን ወይም ቸልተኝነትን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የልጆች ደህንነት ጥበቃ አገልግሎት ክፍል ለማሳወቅ 24/7 ሪፖርት የሚቀበል የስልክ መስመር።

ለአደጋ ተጋላጭ ጎልማሶች የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጎልማሶች ጥበቃ አገልግሎት 240-777-3000፣ 240-777-4815 TTY
በአዋቂዎች ላይ የሚጠረጠር ጥቃትን እና ቸልተኝነትን ሪፖርት ለማድረግ 24/7 ክፍት የሆነ የስልክ መስመር።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ መምርያ የልዩ ተጠቂዎች ምርመራ ክፍል (24 ሰዓት) ስልክ፡- 240-773-5400
በልጆችና በጎልማሶች ላይ የሚፈጸሙ የወሲብ ወንጀሎችን፣ የአካል ጉዳተኛ ልጆችን፣ ሸሽተው፣ የጠፉ ልጆች፣ ከባድ የቤት ውስጥ ጥቃት፣ የተጋላጭ አረጋውያን ጥቃት/አደጋ በአዋቂዎች ላይ የሚደርስ በደል፣ እና የተመዘገበ ሪከርድ ያላቸው የወሲብ ጥቃት ወንጀለኞችን ለሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ መምሪያ ለማሳወቅ 24/7 የስልክ መስመር።

የሞንጎሞሪ ካውንቲ ፖሊስ፡-
የአደንዛዥ ዕፅ እና የወሮበሎች (ጋንግ) የጥቆማ መስመር። 240-773-ወሮበላ (GANG (4264) ወይም 240-773-አደንዛዥ እፅ (DRUG) (3784)
በሞንትጎመሪ ካውንቲ ውስጥ ህገ-ወጥ እጽ ማዘዋወር/የወሮበሎች ቡድን (ጋንግ) እንቅስቃሴዎችን የሚመለከት ማንነት ሳይገለጽ ጥቆማ ለማቅረብ 24/7 ክፍት የስልክ መስመር።

## MCPS ሪሶርሶች

ካውንቲ አቀፍ የተማሪ አመራር
www.montgomeryschoolsmd.org/departments/student-leadership

ዳይሬክተር፣ የተማሪ አመራር እና ከመደበኛ ትምህርት ውጭ የሚከናወኑ እንቅስቃሴዎች 240-740-4692

ተማሪ የቦርድ አባል
www.montgomeryschoolsmd.org/boe/members/student.aspx

የትምህርት ቦርድ ጽ/ቤት ስልክ፡- . . . . . . . . 240-740-3030

የትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ ዋና ኃላፊ . . 240-740-3100

ተባባሪ ሱፐርኢንተንደንት፣ ደህንነት፣ መማር እና ስኬት . .240-740-5630
ስለ ሰክሽን 504 ውሳኔ እና አፈጻጸም 240-740-3230

## የሞንትጎመሪ አስቸኳይ ላልሆኑ ጉዳዮች መገልገያዎች (ሪሶርሶች)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፖሊስ አስቸኳይ ላልሆነ ጥሪ የስልክ መስመር 301-279-8000

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች የመረጃ መስመር
የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ አጠቃላይ መረጃን ያነጋግሩ 311, 301-251-4850 TTY
ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪዎች ውጭ240-777-0311

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ጊዜ ማስታወቂያዎች

በዚህ ድረ-ገጽ አማካይነት ከ MCPS ጋር ሁልጊዜ መገናኘት ይችላሉ፡- www.montgomeryschoolsmd.org
አጠቃላይ ተቋሙን የሚመለከት መረጃና የአስቸኳይ ሁኔታ ማስታወቂያዎችን ለማግኘት፡-

ትዊተር፡- MCPS on Twitter . . www.twitter.com/mcps
ትዊተር በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español www.twitter.com/mcpsespanol

MCPS ፌስቡክ፡- www.facebook.com/mcpsmd
ፌስቡክ በስፓንሽኛ፡- MCPS en Español . www.facebook.com/mcpsespanol

የማንቃት/የማስጠንቀቅ መልክቶች፡- Alert MCPS . . .www.montgomeryschoolsmd.org/alertMCPS

988 SUICIDE & CRISIS LIFELINE

988 LÍNEA DE PREVENCIÓN DEL SUICIDIO Y CRISIS

## MCPS መረጃ እና የአስቸኳይ ክስተት ማስታወቂያዎች (የቀጠለ)

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ፈጣን መልክቶች፣ ኢሜይል መልክቶች እና ዘገባዎች - MCPS QuickNotes Email Messages and Newsletter . www.mcpsQuickNotes.org

MCPS የመረጃ አገልግሎትን ይጠይቁ፡-
ስልክ . . . . . . . . . . . . . . . 240-740-3000
የስፓንሽኛ አስቸኳይ የስልክ መስመር. . . . . 240-740-2845
Email . . . . . . . . . . AskMCPS@mcpsmd.org

MCPS የማህበረሰብ መረጃ ቢሮ 240-740-2837
ቴሌቪዥን፡ MCPS Television . www.mcpsTV.org; Comcast 34, 998; RCN 89, 1058; Verizon 36

በድምፅ የተቀረጸ የአስቸኳይ ጊዜ እና የአየር ሁኔታ መረጃ . . . . . . . . . . . . 301-279-3673

## MCPS ሪሶርሶች የሚገኙበት ድረ-ገጽ
www.montgomeryschoolsmd.org

ዳሰሳ ወይም ቅኘት፡-

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ት/ቤቶች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሰራተኞች የመረጃዎች ዝርዝር ማውጫ

MCPS ስልታዊ (ስትራቴጂያዊ) እቅድ

አትሌቲክስ

Be Well 365

የትምህርት ቦርድ
ጉልበተኝነት፣ ጥቃት/ትንኮሳ፣ ዛቻ/ማስፈራራት

የአውቶቡስ መስመሮች

የልጅ ማጎሳቆል እና ቸልተኝነት

የኮሌጅ እና የሙያ ማዕከል

የግንዛቤ ትምህርት Common Sense Education

የኮርስ ጥንቅር መግለጫ

የማህበራዊ ሚዲያዎችንና ሌሎች የዲጅታል መሳሪያዎችን ኃላፊነት በተሞላበት መንገድ መጠቀምና የኢንተርኔት ደህንነት - Cybercivility and CyberSafety

የዲፕሎማ መስፈርቶች

ወሮበሎች (ጋንግ) እና የወሮበሎች ተግባር

## MCPS የሪሶርስ ድረ-ገጽ (የቀጠለ)
www.montgomeryschoolsmd.org

የውጤት አሰጣጥና ሪፖርት አቀራረብ

የሃይማኖት ብዝሃነትን የማክበር መመርያዎች

ስለ ተማሪ ጾታዊ ማንነት መገለጫ መመሪያ

ምሣ የምግብ ዝርዝር

የሜሪላንድ 2ኛ ደረጃ ት/ቤት ምዘናዎች

ፀረ-መድሎ

በኦንላይን የመመረቂያ ፈለግ

የሰዉነት ማጎልመሻ ትምህርት

መርኖች እና ደንቦች

የስነልቦና አገልግሎቶች

የተማሪ ሠራተኛ አገልግሎቶች

የልጅ መበደል እና ቸልተኝነት ሪፖርት ማደረግ

ፍትኃዊ ተሐድሶ

በት/ቤት የካውንስሊንግ እገልግሎቶች

የትምህርት ቤት የጤና አገልግሎቶች

የትምህርት ቤት ደህንነት

ፆታዊ ጥቃት

የማህበራዊ ሚድያ ዲጂታል ሲትዝንሽፕ (Social Media Digital Citizenship)

ልዩ ትምህርት

ልዩ ፕሮግራሞች

ስልታዊ የእቅድ ዝግጅት

የተማሪ ስነ-ምግባር ደንብ

የተማሪ በኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ መማር - eLearning

የተማሪ የግል ገመና

የተማሪ አገልግሎት ትምህርት

ራስን መግደል መከላከል

የሰመር ትምህርት ቤት
Summer School

# መግቢያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች እና ሰራተኞች ሥርዓት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢን ለመጠበቅ በመማር እና በማስተማር ላይ ያተኮረ አወንታዊ የት/ቤት ድባብ ለመፍጠር ይጥራል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ማስተካከያ፣ ሠላም እና ደህንነት እቅድ፣ የባህሪ ማስተካከያ መርኅ መልሶ ማቋቋም፣ ማገገሚያ እና ትምህርት የሚሰጥ፣ ፍትሃዊ እና በፍትሃዊነት በግልፅ እንዲተገበር ያደርጋል። በአካልም ሆነ በቨርቹዋል የትምህርት አከባቢ አወንታዊ የት/ቤት አውድ እንዲኖር ለማድረግ ከMCPS መርህ ጋር የማይጣጣም የተማሪ ባህሪን ለመግታት ተገቢ የሆኑ ባህሪያትን ማስጠበቅ ነው። የቦርድ ፖሊሲ ACA፣ አድልዎ የሌለበት፣ ፍትሀዊነት እና ባህላዊ ብቃት የሚያሳካው "ፍትሀዊ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ማስፈፀምን እና በት/ቤቶች የትምህርት እድልን መፍጠር አንዱ ዋነኛ አካል ማድረግ" ተብሎ የሚጠበቀውን በመተግበር ነው።

የተማሪ የስነምግባር ህግ አላማ ለአዎንታዊ ባህሪ የሚጠበቁ መርሆችን ማእቀፍ መወሰን እና በዲሲፕሊን አተገባበር ላይ ሚዛናዊነት እና ፍትሃዊነትን በግልፅ፣እና በተገቢ ሁኔታ ተከታታይ የባህሪ ማስተካከያ ውጤቶችን ማጎልበት ነው። የተማሪ የስነምግባር ህግ የተማሪዎችን የስነምግባር ጉድለት ለመቅረፍ፣ ለማረም፣ ለማደስ እና ስርዓት ያለው እና ደህንነቱ የተጠበቀ የትምህርት አካባቢን በማስተማር እና በመማር ላይ ያተኮረ የባህሪ ማስተካከያ መርህን ከፕሮቶኮሎች ጋር ያንፀባርቃል። የተማሪን መጥፎ-ስነምግባር ለመቅረፍ የተዘጋጁት ፕሮቶኮሎች ከፌዴራል እና ከስቴት መስፈርቶች እንዲሁም ከቦርድ ፖሊሲዎች እና ከ MCPS ደንቦች ጋር የተጣጣሙ ናቸው።

ይህ የተማሪ የስነምግባር ህግ ቋሚ ሰነድ በመሆኑ፣ MCPS ከተማሪዎች፣ ከወላጆች/ከአሳዳጊዎች፣ ከሰራተኞች እና ከመላው ማህበረሰባችን ጋር በመቀ ናጀት የዲሲፕሊን ተግባሮቻችንን የመማር፣የመከባበር፣ የልህቀት እና ፍትሃዊነት እና የግንኙነት ዋና እሴቶቻችንን ለማንፀባረቅ ቁርጠኛ ነው። ይህ አሠራር እያደገ በመጣው የትምህርት ምርምር ውጤት መሠረት፥ ተማሪዎችን ማገድ ወይም ማባረር፣ የመጨረሻ አማራጭ ካልሆነ በስተቀር የተማሪን ባህሪ ወይም የት/ቤትን ደህንነት በማሻሻል ረገድ ትንሽ ወይም ምንም በጎ ተጽዕኖ እንደማይኖረው ተገልጿል። በተጨማሪ፣ ተማሪዎች ጠቃሚ የትም ህርት ጊዜ ባጡ ቀጥር፣ ስኬታማ ለመሆን ይበልጥ አስቸጋሪ እየሆነባቸው እንደሚሄድ እናውቃለን። የ MCPS የረዥም ጊዜ የፍትሃዊነት ቁርጠኝነት ላይ በመመስረትና ከሜሪላንድ ሕግ ጋር በማጣጣም፣ MCPS የትምህርት ቤቶቻችንን ህይወት የማደስ ተሞክሮዎችን እና ፍትህን የማሳካት ባህል የማስፈን ሥራውን ቀጥሏል። የተሻሻለ የመማሪያ ክፍል እና የት/ቤት አስተዳደርን የማጎልበት ጥረታችንን ለማስፋት ሪሶርሶችን ለማግኘት፣ እና ለሠራተኞችም ሆነ ለተማሪዎች የሙያ እድገት መርሃ ግብር እና የክህሎት ማሻሻያ እንቅስቃሴዎችን ለማሟላት ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በመተባበር ለመሥራት MCPS ቁርጠኛ ነው። MCPS ተማሪዎች ከስህተታቸው እንዲማሩ እና ባህሪያቸው ሌሎችን በሚነካበት ጊዜ ተገቢውን ማስተካከያ እንዲደረግ ይፈልጋል።

ሁሉም-ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ ሰራተኞች በአንድነት ሲተባበሩ፣ የመደጋገፍ እሴት ሲኖራቸው፣ እና የእያንዳንዳቸውን ሚና ሲያከብሩ፣ እና ሁሉም በመከባበር አብረው እንዲሠሩ በሚያስችላቸው የጋራ ትክክለኛውን የባህሪ ማስተካከያ ሲያዳብሩ MCPS በጣም ስኬታማ እንደሚሆን እናምናለን። በመማር - ማስተማር ላይ ያተኮረ ሥርዓት እና ደህንነቱ የተጠበቀ የመማሪያ አውድ ይገነባል።

## ■ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) የሥነሥርዓት አከባበር መርህ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ማስተካከያ፣ ሠላም እና ደህንነት እቅድ፣የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ትምህርት ቤቶች አወንታዊ፣የመከባበር፣ሥርዓት እና ደህንነታቸው የተጠበቀ የትምህርት አከባቢዎች ውጤታማ ትምህርት ለማግኘት አስፈላጊ ይሆናሉ የሚለውን መርህ ይደነግጋል። የተማሪዎችን ተሳትፎ ማሳደግ፣ የተማሪዎችን ስኬት ማሳደግ፣እና በተቻለ ጊዜ ከመከሰቱ በፊት የተማሪዎችን እኩይ ተግባር የሚከላከሉ አወንታዊ የት/ቤት ባህሎችን እና የት/ቤት ድባብ ሁኔታዎችን ማሳደግ።

ተማሪዎች ከቤታቸው በተጨማሪ፣ ትምህርት ቤቶች መልካም ባህርይ፣ አርአያነት፣ እና የጋራ መከባበር እና ክብር መስጠት፣ የሚጠበቅበት ማህበረሰብ ሲህን ስኬታማ ትምህርትን ለመቅሰም በእጅጉ አስፈላጊ ነው።

ጤነኛ፣ ውጤታማ አዋቂዎች ሆነው እንዲያድጉ፣ ተማሪዎች መከባበር የሰፈነበት የመማሪያ ምህዳር ይፈልጋሉ፣ ይሄም ማለት እያንዳንዱ ሰው ዋጋ ያለው የማህበረሰብ አባል የሆነበት እና ይሄን ለመፍጠር እና ለማስቀጠል በጎ አስተዋፅዖ እንደሚኖረው የሚታ መንበት ነው። ማህበረሰቡ ሲበጠበጥ፣ የትምህርታዊ መሪዎች የሚሹት ለመረዳት፣ ለማሳወቅ እና ለመበጥበጡ መሰረታዊ መንስ ኤዎች መፍትሄ መስጠት ነው፣ የመማሪያ ምህዳሩ ወደ ቀድሞ ሁኔታው ይመለሳል፣ እና ተማሪዎች ከስህተቶቻቸው የሚማሩበት አጋጣሚዎች ይሰጣቸዋል፣ በባህሪያቸው የተነሳ ማንኛውንም ጉዳት ማስተካከል፣ እና በአሳዩት ባህሪ የተነሳ የተዛቡ ግንኙነቶችን ወደ ቀድሞ ሁኔታቸው መመለስ ነው።

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የዲስፕሊን እርምጃ አወሳሰድን በተመለከተ ተማሪዎች ከስህተቶቻቸው እንዲማሩ፣ በባህርያቸው ምክንያት የሚፈጠሩ ማናቸውንም ጉዳቶች ለማረም፣ እና በባህርያቸው ምክንያት የተስተጓጎለውን ግንኙነት ወደ መልካም ሁኔታ ለመመለስ በሚያስችላቸው ግንኙነት ላይ ያተኮረ አቀራረብ ይጠቀማል።

MCPS ተገቢ ባህሪን መማር የእድገት ሂደት በመሆን የተማሪዎችን የተለያዩ የባህሪ እድገት ፍላጎቶችን ደረጃቸውን በጠበቁ ምላሾች እና ማስተካከያዎችን ከመፍጠሪያ ውጤታማ ስልቶች ጋር የሚጣመር እንደሆነ ያምናል። ተከታታይ የማስተማሪያ ስልቶች እና የስነምግባር ግብረመልሶች ለማስተማር እና መማር ድጋፍ ሰጪ፣ አዎንታዊ ባህሪዎችን የሚያበረታታ፣ እና የመልሶ ማገገም ዲሲፕሊን መርኖንም/ፍልስፍናን የሚያንፀባርቅ ነው። ቀድሞ ወደነበረበት የመሻሻል ሁኔታ የመመለስ ተግባሮች የመከላከል እና አስቀድሞ የጥንቃቄ እርምጃ መውሰድ ናቸው፤ ጠንካራ ግንኙነትን መገንባት ላይ በማተኮር የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ደህንነት ለመጠበቅ የሚያስችሉ ባህርያትን በግልጽ መደንገግ፤ እና የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ደህንነት ለመጠበቅ በግልጽ የተቀመጡ ስነ ምግባራት ስጋት በሚያስከትሉ መንገድ ሲጣሱ እርምጃ መውሰድ፤ ችግር ፈጣሪ በሆነ ባህርይ ምክንያት ለሚፈጠሩ ማንኛውም አይነት ጉዳቶች ተጠያቂነት ላይ ማተኮር፤ እና ተጎጂ በሆነው አካል ፈቃደኝነት እና ትብብር በአስቸጋሪ ባህርይ ምክንያት የተበላሹ ግንኙነቶችን የማደስ መንገዶችን መቀየስ ዋና የትኩረት አቅጣጫ ይሆናል።

የትምህርት ቤት የባህሪ ማስተካከያ ተሞክሮዎቻችን የተነደፉት በመማሪያ ክፍል እየተማሩ የሚገኙ ተማሪዎች ከ MCPS ኮሌጅ እንዲመረቁ እና የሙያ ዝግጅት እንዲኖራቸው ነው።

የማንኛውም ባህሪ ማስተካከያ ተቀዳሚ አላማ ማገገሚያ፣ ወደ ቀድሞ መመለሻ፣ አስተማሪ በመሆን መተግበር በሚቻለው ከፍተኛ መጠን ድረስ ተማሪዎች በመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ውስጥ እንዲቀጥሉ የሚያስችል ነው። አሉታዊ ስነ-ምግባር እየተባባሰ/እየጨመረ እየተስፋፋ እንዳይሄድ አግባብነት ያለው ለመማር ምቹ የሆነ እና አካደሚያዊ ስኬትን የሚደግፍ አዎንታዊ አካባቢን ለመጠበቅ የተነደፈ የተደረገ የማርገብ ስልቶችን/ስትራቴጂዎችን እና ቴክኒኮችን በመጠቀም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የስነምግባር ማስተካከያ በቅደም ተከተል ይተገብራል። እገዳዎችና ስንብቶች እንደ የመጨረሻ አማራጮች ብቻ መሆን አለባቸው።

## ■ የተማሪ ስነምግባር

ተማሪዎች በትምህርት ቤት፣ በት/ቤት ስፖንሰር በተደረጉ ዝግጅቶች፣ በ MCPS አውቶቡሶች እና በሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች ላይ እራሳቸውን እንዴት መምራት እንዳለባቸው የሚጠበቅባቸውን ስነ-ሥርዓት እንዲያውቁ ይደረጋል። ብዙ መምህራን የክፍል ሥነ ምግባር ደንቦችን በማዳበር ሂደት ውስጥ ተማሪዎችን በቀጥታ ያሳትፋሉ፣ ተማሪዎች ከሌሎች ጋር እንዴት መግባባት እንደሚችሉ እና ከሌሎችስ እንዴት እንደሚጠብቁ የሚስማሙበት አስፈላጊ ስነ-ስርአት ይገነባሉ።

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ተማሪዎች እርስ በርስ በአክብሮትና እና በመከባበር ድባብ የሚጠበቁ አዎንታዊ ስነምግባርን በማስቀመጥ ሂደት ውስጥ የሚሳተፉበት መነሻ ነጥብ ነው፡-

1. የራሴ ቃላት፣ ተግባር፣ እና አቋም/አመለካከት በማንኛውም ጊዜ ለራሴና ለሌሎች ያለኝን ክብር ይገልፃሉ።
2. በሰዓቱ ወደ ት/ቤት በመምጣት/በወቅቱ በመድረስ፣ በስነስርአት በመልበስ፣ እና በትምህርቴ ለማተኮር ዝግጁ በመሆን በራሴ፣ በወደፊቴ እና በት/ቤቴ ያለኝን አክብሮት/ከበሬታ/ኩራት አሳያለሁ።
3. ሁልጊዜ የምፈልገው ግጭቶችን ለመፍታት ይበልጥ ሰላማዊ መንገዶችን ሲሆን፣ ግጭቶችን በገዛ ራሴ በሰላም ልፈታቸው ካልቻልኩ የመምህራንን፣ አስተዳዳሪዎችን፣ ወይም የት/ቤት ሰራተኞችን እርዳታ ማግኘት እፈልጋለሁ።
4. በሌሎች የት/ቤት ማህበረሰብ ላይ ያደረስኩትን የሆነ ጉዳት/በደል ለማረም ዝግጁ እሆናለሁ።
5. ሰላማዊ እና ንፁህ የመማርያ አካባቢ በት/ቤቴ በማራመድ ኩራት/ከበሬታ ይሰማኛል።

## ■ የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ስራተኛ ሀላፊነቶች

የ MCPS ሰራተኞች ለሁሉም ተማሪዎች እና ጎልማሶች፥ በጎነት ያለው፣ አጋዥ የሆነ፣ ደህንነቱ የተጠበቀ እና ማራኪ የሆነ፣ ለመማር ማስተማር ምቹ የትምህርት ቤት አካባቢዎችን ለመፍጠር ይተጋሉ። እነሱ ከተማሪዎች ጋር ጠንካራ ግንኙነቶችን ለመገንባት ትልቅ ሚና የሚጫወቱ በት/ቤቶች ውስጥ ተንከባካቢ አዋቂዎች ይሆናሉ፤ ይህም ተማሪዎች ከት/ቤት ጋር ያላቸውን ግንኙነት የሚያመቻች እና የሚያደናቅፉ ተግባራት ውስጥ የመሳተፍ እድሎችን ይቀንሳል። ሁሉም የት/ቤት የስራ ባልደረቦች ከተማሪዎች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነቶች/መቀራረብ እንዲኖራቸው በተለያዩ መንገዶች ይጥራሉ፣ ምክንያቱም በት/ቤታቸው ከአዋቂዎች ጋር ትርጉም ያለው ግንኙነቶች ያሏቸው ተማሪዎች በትምህርት ክፍል ረባሽ የመሆን፣ የመቅረት፣ ወይም ት/ቤት ጥሎ የመሄድ አዝማሚያቸው ያነሰ ነው።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) የስራ ባልደረቦች የሚከተሉትን ያከናውናሉ፡-

1. ለተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን ስነምግባር በግልፅ ያስቀምጣሉ፤ ትምህርት ሰጭ የተግሣጽ አቀራረብም ይወስዳሉ/ይከተላሉ።
2. የተማሪዎችን አወንታዊና ተገቢ ስነምግባር መሸለምና እውቅና መስጠት።
3. በዲሲፕሊን ውስጥ አድልዎ እና አለመመጣጠንን ለመለየት እና ለማስወገድ ይጥራሉ እና የዲሲፕሊን ህጎችን ቀጣይነት ባለው ፍትሃዊነት እና በእኩልነት ይተገብራሉ።
4. ቤተሰቦችን፣ ተማሪዎችን፣ የስራ ባልደረቦችን/ሰራተኞችን፣ እና ማህበረሰቡን አወንታዊ ስነምግባር እና የተማሪን ተሳትፎ በማሳደግ ሂደት ማሳተፍ።
5. ግልፅ የሆነ፣ ለእድገትና ለእድሜያቸው የሚመጥን/አግባብ የሆነ ስነምግባርን ማበረታታት እና በስነምግባር ብልሹነት/ጉድለት ተመጣጣኝ ርምጃዎችን በመውሰድ ለሁሉም ተማሪዎቸ እድገትና የመማር እድል በሚደግፍ አኳኋን መተግባራቸውን ማረጋገጥ።
6. የአካል ጉዳት ላላቸው ተማሪዎች፣ ተገቢ ቅደምተከተሎች እና ለሁሉም፣ከፌደራልና ከስቴት ህጎች/ተፈላጊዎች ጋር የሚጣጣሙ የፍርድ ሂደቶችን ማካተት።
7. ተማሪዎችን ከመማርያ ክፍል ማስወጣት እንደ መጨርሻ አማራጭ ብቻ መወሰድ ይኖርበታል፣ እናም ተማሪዎችን በተቻለ ፍጥነት ወደ ክፍል እንዲመለሱ ማድረግ።

## ■ የወላጅ/አሳዳጊ እና የማህበረሰብ ሃላፊነቶች

ወላጆች/አሳዳጊዎች ከልጆቻቻው ጋር በት/ቤት ሊኖር ስለሚገባ ተገቢ ስነምግባር ያነጋግሯቸው እናም አወንታዊ፣ የጥሩ ስነምግባር ደጋፊ፣ ሰላማዊ፣ እና ጥሩ ባህርይን የሚጋብዝ ለማስተማርና ለመማር ምቹ የሆነ የትምህርት ቤት አካባቢ በመፍጠር ልጆቻቸው ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ልጆቻቸውን ያግዟቸው።

ልጆቻቸው ሊያጋጥማቸው በሚችል የባህሪ ችግሮች እና በልጃቸው ላይ የተቃጡ ችግሮችን ለመፍታት ወላጆች/አሳዳጊዎች ከ MCPS ሰራተኞች ጋር በትብብር መስራት አለባቸው።

ወላጆች/አሳዳጊዎች ከት/ቤቶች ጋር በመተባበር በት/ቤትና ማህበረሰብ ውስጥ የምክር አገልግሎት፣ ከመደበኛ ትምህርት በኋላ የሚካሄዱ ፕሮግራሞች፣ እና የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች ወደ መሳሰሉ ደጋፊ ቡድኖች ወይም ፕሮግራሞች ልጆቻቸው እንዲሳተፉ በማገዝ ማደፋፈር/መስራት አለባቸው።

የሞንትጎሞሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS ) ቀና የሆነ፣ ሰላም የሰፈነበት፣ አጋዥነት ያለው፣ እና ጋባዥ የሆነ ሁኔታ/የትምህርት አካባቢ በመፍጠር የሚያግዙ የማህበረሰብ ድርጅቶችን ከት/ቤቶች ጋር መጎዳኘት እንዲችሉ ያበረታታል። አረአያነት ያለው ድጋፍ ሰጭ አገልግሎት፣ በምክርና በማሰልጠን አገልግሎት እንዲሁም ልዩ ልዩ ለት/ቤት መጠቀሚያ ነገሮችን በመለገስ የት/ቤት የስራ ባልደረቦች የማገገሚያ ልምምዶችን በመተግበር እና

ቀጣይነት ያለው የተማሪዎች ስነምግባርን ለማነጽ እዚህ ላይ በተገለጸው የተማሪ ስነምግባር መመርያ ጋር የሚጣጣምድጋፍ እንዲሰጡ ያደፋፍራል።

## ■ የመልሶ ማገገሚያ/ማደሻ ተግባር/ልምምድ፣ የመልሶ ማገገሚያ/ማደሻ  ፍትሕ፣ የመልሶ ማገገሚያ/ማደሻ  ት/ቤቶች

ከጁላይ 1, 2019 ጀምሮ፣ የትምህርት ቤቶች የዲሲፕሊን ስርአትና ደንቦች አዳሽ እና ጠጋኝ አቀራረቦች መሆን እንዳለባቸው የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል።ህጉ የማንኛውንም የዲሲፕሊን እርምጃ ዋና አላማ ጠጋኝ፣ የሚያድስ እና ትምህርታዊ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል—

- ዘዴዎቹ በዋነኝነት በንቃት ቀድሞ መከላከል መሆን አለባቸው፣
- በግንኙነቶች እና በሚጠበቁ ነገሮች ላይ አጽንዖት ይሰጣል፣
- ለሚደርሰው ጉዳት የተጠያቂነት ምላሽ ይኖራል፣ እና
- ግንኙነቶችን የማደስና የመጠገን ትኩረት አለው።

MCPS ለፍትሃዊነት ያለውን ቁርጠኝነት በመገንባት ፍትሃዊነትን፣ የመልሶ ማቋቋም ተግባራትን፣ የፍትኃዊ ተሃድሶን እና በአሰቃቂ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ጉድለትን ማረም እና ተሀድሶን የትምህርት ቤቶቻችን ባህል፣ የትምህርት ቤቶችን ድባብ እና የሚጠበቁ ነገሮች ለማካተትና ለመገንባት መስራታችንን እንቀጥላለን።

የተኃድሶ እና የማገገሚያ ልምዶች ለሰራተኞች እና ለተማሪዎች በተከታታይ የመከላከል፣ በንቃት ምላሽ ሰጪ እርምጃዎችን የሚያካትቱ እና በግንኙነት ላይ ያተኮሩ ሂደቶች ናቸው። እነዚህ ሂደቶች አንድ ላይ ጤናማ ግንኙነቶችን ይገነባሉ እንዲሁም የማህበረሰቡን ስሜት እና ቁርጠኝነት ይፈጥራሉ። ይህ ግጭትን እና ያልተገባ ድርጊትን እንደሚከተለው ለመከላከል እና ለመፍታት ይረዳል፡-

1. የተጎዳውን ማህበረሰብ ማካተት እና ኃላፊነት ማጎናፀፍ፤ ሆኖም ተሳትፎ ሁል ጊዜ በፈቃደኝነት ላይ የተመሠረተ ነው።
2. በተለይ በስህተት ድርጊት ዙሪያ ሚናዎቻቸውን፣ አመለካከቶቻቸውን፣ እምነቶቻቸውን እና ባህሪያቸውን ለመመርመር የሚሳተፉትን ሁሉ አስተሳሰብ መፈተሽ ተገቢ ነው።
3. ማህበረሰቡን በንቃት የመገንባት ስልቶችን መጠቀም፣ ተፈላጊ የማህበረሰብ ድርጊቶችን እና ባህሪያትን ማወቅ እና ማክበር፣ እና ከማህበረሰቡ የሚጠበቁ ነገሮችን ማቋቋም።

የተኃድሶና ማገገሚያ ልምምዶች የባህሪ ማስተካከያ መዘዞችን አስፈላጊነት አይፃረሩም፣ ይልቁንም ለተጎዱት ሰዎች ትርጉም በሚሰጥ መልኩ ጉዳታቸውን ለመጠገን በሚሰሩበት ወቅት ተማሪዎች አመለካከታቸውን እና ባህሪያቸውን እንዲመረምሩ ያስችላቸዋል።

ከቦርድ ፖሊሲ "Board Policy ACA" ጋር በማጣጣም  ከአድሎአዊነት የነፃ፣ ፍትኃዊነት፣ እና ባህላዊ ብቃት ፣ የትምህርት ቤት የደህንነት እርምጃዎች በተማሪዎች ላይ ማንነታቸውን መሠረት ያደረገ፣ ወይም በትክክለኛ የግል ማንነታቸው ባህርይ ምክንያት የተዛባ አመለካከትን መተግበር የለባቸውም። የተሃድሶ ተሞክሮዎች በታማኝነትና በትክክለኛነት ሲተገበሩ፥ አመራርንና መማር ማስተማርን የሚያበረታታ እና የሚደግፍ አወንታዊ የትምህርት ቤት አውድ ይፈጥራሉ።

ፍትኃዊ ተሃድሶ የአንድ ትምህርት ቤት ማህበረሰብ አባላትን የሚገዳደር ፍልስፍና ነው—

1. ስለተጣሰው ህግ ወይም ደንብ ላይ ከማተኮር ይልቅ በመጥፎ ድርጊት ምክንያት የደረሰ ጉዳት ላይ ነው የሚያተኩረው፤
2. ጉዳት የደረሰባቸውን ማበርታት እና በዲሲፕሊን ሂደቱ ውስጡ ለፍላጎቶቻቸው በእኩል መጠን እንደሚታሰብ ማሳየት፤
3. ሌሎችን የጎዱ ግለሰቦችን መደገፍ፣ ለድርጊታቸው የግል ሃላፊነት እንዲወስዱ እና የደረሰውን ጉዳት እንዲገነዘቡ፣ እንዲቀበሉ እና በእነርሱ ምክንያት ለተፈጠረው ጉዳት ኃላፊነት ወስደው ግዴታቸውን እንዲያሟሉ ማበረታታት፣
4. ቅጣትና ማግለል ላይ ከማተኮር ይልቅ ትብብር እና አብሮነትን ማበረታታት፤
5. ሌሎችን የጎዱ ግለሰቦች ያስከተሉትን ተፅዕኖ በመረዳት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ፣ እና
6. አካላዊ ግጭቶች ወይም በዲሲፕሊን ምክንያት ከማህበረሰብ ርቀው የነበሩ የማህበረሰብ አባላት መልሶ መቀላቀል የመሰሉ የት/ቤትን ማህበረሰብ ሊፈትኑ የሚችሉ ሁኔታዎችን መገመት እና መፍታት።

ፍትኃዊ ተሐድሶ፡- በተፈጸመ ጥፋት፣ የተጣሱ ሕጎች እና ቅጣት ላይ ያተኮረ የዲስፕሊን አካሄድ ብቻ ከመጠቀም በተቃራኒ፤ ፍትኃዊ ተሃድሶ ሦስት በጣም የተለያዩ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፡-

1. የተጎዳው ማነው?

2. ጉዳት የደረሰባቸው /የጥቃቱ ሰለባ የሆኑት  የሚያስፈልጋቸው ምን እንደሆነና የደረሰውን ጉዳት ለመጠገን ምን ርምጃ ነው መወሰድ ያለበት?

3. የሚያስፈልጋቸውን ነገሮች ለማሟላት፣ የደረሰውን ጉዳት ለመጠገን፣ እንዲሁም ግንኙነት እንዲቀጥል ለማድረግ ኃላፊነት ያለበት ማነው?

ፍትኃዊ ተሃድሶ የተለየ ፕሮግራም ወይም ሥርዓተ ትምህርት/ካሪኩለም አይደለም። ጭብጡን ለመቀበል፣ለትግበራ እና ለማዋሃድ ትጋትን የሚጠይቅ የአስተሳሰብ ለውጥ ነው። ይህ አእምሮአዊ የአስተሳሰብና የአመለካከት ለውጥ ትኩረቱ በመልካም ግንኙነት፣ ትብብር፣ እና በተማሪዎች መካከል፣ በሠራተኞች፣ በቤተሰቦች፣ እና በአጠቃላይ የትምህርት ቤት ማህበረሰብ መካከል የእርስበርስ ተሳትፎ የሰፈነበር እውነተኛ ፍትሃዊ የትምህርት ቤት ማህበረሰብን ለመፍጠር  በጣም አስፈላጊ ነው።

MCPS ለሁሉም ትምህርት ቤት-ተኮር ሰራተኞች ህግና ደንብ፣ ሥርዓት የማክበር አካል ተደርጎ ስለ ተሐድሶ አቀራረብ  ዲስትሪክት አቀፍ ስልጠና እንዲወስዱ ያደርጋል።በየትምህርት ዓመቱ ፍትኃዊ ተሃድሶን ሙያዊ እድገት፣ ትግበራ እና ግምገማ ለማስቀጠል በህንፃዎቻቸው ውስጥ የፍትኃዊ ተሃድሶ አሰልጣኝን ለማዘጋጀት እያንዳንዱ ትምህርት ቤት መደበኛ ክፍያ ያገኛል።

በእኛ እምነት እና በምርምርም የተደገፈ በመሆኑ፣ የተሐድሶ አቀራረብ በተማሪዎች መካከል ያለውን ተደጋጋሚ መቅረት የሚቀንስ እና  ሰራተኞች እና ተማሪዎች የሚተልሙትን ደህንነቱ የተጠበቀ እና ጤናማ ማህበረሰብ ይገነባል።

# የቅደም-ተከተል ሂደቶች ግዴታዎች

## ■ የተማሪዎች ስነምግባር ኮድ አፈጻጸም

በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የተደነገገው የስነምግባር ማስተካከያ የሚያስከትለው መዘዝ የተማሪ የስነምግባር ህግ ተማሪዎች MCPS ንብረት ላይ እያሉ ወይም MCPS ዝግጅት ላይ በሚገኙበት ጊዜ በሁሉም ጊዜ ላይ ተፈጻሚ ይሆናል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ንብረት ማለት፡- የትኛውንም የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ትምህርት ቤት፣ ወይም ሌላ የ MCPS ተቋምን፣ በ MCPS ባለቤትነት የሚተዳደሩ ቦታዎችን ጨምሮ፣MCPS አውቶቡሶች እና ሌሎች የ MCPS ተሽከርካሪዎች ወይም በ MCPS የሚደገፉ ተማሪዎችን የሚያሳትፉ እንቅስቃሴዎችን ያካትታል። ከትምህርት ሰዓት ውጭ እና ከት/ቤት ንብረት ርቆ የሚፈጸም የተማሪ ስነምግባር በትምህርት ቤት የተማሪዎችን ወይም የሰራተኞችን ጤንነት ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ፣ ወይም ስነምግባሩ መንስኤ ከሆነ ወይም ከፍተኛ መሰናክል ያስከትላል ተብሎ ከታመነ፣ ወይም በትምህርት ቤት እንቅስቃሴዎች ላይ ቁሳዊ አደጋ ሊያስከትል ይችላል ተብሎ የትምህርት ቤቱ ርእሰመምህር ካመነ(ች)በት የዲሲፕሊን እርምጃ ሊያስወስድ ይችላል።

የባህሪ ማስተካከያ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ እና ተገቢ መሆን እና የተማሪን ትምህርት እና እድገት የሚያበረታታ መሆን አለበት። የዚያ እርምጃ አካል በሆነ መንገድ ተማሪው/ዋ አካዴሚያዊ ስራ ማከናወን ካለበት/ባት፣ ግቡ ከተያያዘው ትምህርት ጋር የተዛመደ አንድ ዋጋ ያለው ትምህርት እንዲማር/ድትማር ማድረግ ነው። ነገር ግን ለቅጣት ብቻ የታለመ መሆን የለበትም ተማሪው ቢያውቅም ባያውቅም አስተማሪው(ዋ) እንደዚህ ዓይነቱን ሥራ በምክንያትነት መስጠት አይችልም/አትችልም። አሰልቺ የድግግሞሽ ስራም እንደመቅጫ አይፈቀድም። አንድ/ዲት አስተማሪ አንድን ተማሪ አንድ አረፍተነገር ደጋግሞ/ማ እንዲ(ድት)ፅፍ ወይም ከመዝገበ ቃላት እንዲ(ድት)ገለብጥ ማድረግ የለበ(ባ)ትም። የአንድ ተማሪ ትግባሬዎች ለምን ልክ እንዳልነበሩ የሚገልፅ መጣጥፍ መፃፍ አንድ ተቀባይነት ያለው አካዴሚያዊ እርምጃ ነው።

የትምህርት ውጤቶች መቼም ቢሆን ማስተካከያ የማይደረግባቸው እንደ ባህሪ ማስተካከያስለሚቆጠር ነው። ቢሆንም፣ በMCPS ደንብ IKA-RA መሰረት፣ የክፍል/የፈተና ውጤት አሰጣጥና ሪፖርት "Grading and Reporting"፣ አንድ/አንዲት ተማሪ በአካዴሚያዊ ማጭበርበር ላይ ከተገኘ/ች፣ መምህሩ ዜሮ ሊሰጠው/ጣት ይችላል።

የእረፍት ጊዜ ሊከለከል የሚችለው በዋናው/በተወካዩ ውሳኔ ለተማሪው(ዋ) ደህንነት አሳሳቢ በሚሆንበት ጊዜ (የሥራ መሣሪያዎች ወይም ተቋሙ ጥገና እየተደረገ ባለበት ወቅት፣ ወይም ከባድ የአየር ሁኔታ ባለበት ሁኔታ) እና/ወይም አንድ ልጅ በራሱ(ሷ) ወይም በሌሎች ላይ ጉዳት የማድረስ አደጋ ላይ ሲወድቅ ብቻ ነው። በተጨማሪ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች ምግብ ወይም ከምግብ ጋር የሚገናኙ ማበረታቻዎችን በዲስፕሊን ቅጣት ምክንያት አያግዱባቸውም።

ጥቂት የቡድን አባላት በፈፀሙት ድርጊት ምክንያት የቡድናቸው አባላት ተማሪዎች በሙሉ ሊቀጡበት አይችሉም። ለምሳሌ፣ አንድ ተማሪ ክፍል ውስጥ ቢ(ብት)ረብሽ፣ አስተማሪው/ዋ በክፍል የሚገኙትን ተማሪዎች በሞላ በጊዜያዊነት ማገት አይ(ት)ችልም። ለትግባሬው ተጠያቂው ሰው ባይታወቅም ይህ ህግ የፀና ይሆናል።

አንድ/ዲት ተማሪ ምንግዜም/በፍፁም በአካል መቀጣት የለበ(ባ)ትም። ነገር ግን በሜሪላንድ ህግ መሠረት፣ በትምህርት ቤት ቅጥር ጊቢ ውስጥ ወይም ትምህርት ቤት በሚያሠራው ጉዞ ላይ ድብድብን ለማስቆም፣ ረብሻን ለመከላከል፣ ወይም አደናቃፊ ተማሪን ለማገድ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ሠራተኞች [1] ተመጣጣኝ የሆነ ሃይል መጠቀም ይችላሉ። በ MCPS ደንብ JGA-RA የትምህርት ክፍል አስተዳደር እና የተማሪዎች የባህሪ ማስተካከያዎች ድንጋጌ ከተጠቀሱት ውስን ሁኔታዎች በስተቀር፣ MCPS ውስጥ የአካል እንቅስቃሴን መገደብ ወይም ማገድ የተከለከለ ነው። ጁላይ 1፣2022 ተግባራዊ የሆነ፣ በሁሉም ፐብሊክ ት/ቤቶች ውስጥ በማንኛውም ሁኔታዎች ማግለልን/መነጠልን መጠቀምን የሜሪላንድ ህግ በግልፅ ይከለክላል።

[1] ተመጣጣኝነት ያለው ኃይል ማለት ምን እንደሆነ በ "MCPS Regulation COB-RA" ክስተትን ሪፖርት ስለማድረግ -Incident Reporting በሚለው ደምብ ላይ ይበልጥ ተዘርዝሯል።

## ■ የባህሪ ማስተካከያ እና ደህንነት ውሳኔዎች ላይ ተፅዕኖ ያላቸው ሁኔታዎች

የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS) ሰራተኞች ግልፅነት የተሞላበት፣ በልጆቹ የእድገት/እድሜ አንፃር ተገቢ መስፈርቶችን በመጠቀም ቅጣቶች ሚዛናዊና ፅኑ መሆናቸውን እያረጋገጡ የባህሪ ማስተካከያ ውሳኔዎችን ያደርጋሉ። አጠቃላይ ሁኔታዎችን በመገምገም፤ የት/ቤት ሠራተኞች "የአፃፋውን ተመጣጣኝነት" ከዚህ በላይ ከተሰጡት ምሳሌዎች ጋር በማስተያየት መገምገምና የሚከተለውን መመዘኛ ከተማሪ ዲስፕሊን ጋር ማገናዘብ ይኖርባቸዋል።

1. የተማሪው(ዋ) ዕድሜ (ከቅድመ መዋዕለ ህጻናት እስከ 3ኛ ክፍል በሚገኙ ተማሪዎች ላይ የእገዳ እና የማባረር ቅጣት በአጠቃላይ ተግባር ላይ መዋል የለበትም)[2]
2. ከዚህ ቀደም የነበሩ አሳሳቢ የዲሲፕሊን ማስተካከያ ላይ ጥፋቶች (ተቀዳሚ ግድፈት አይነት፣ የቀደሙ ጥፋቶች ብዛት፣ እና ለተመሳሳይ ጥፋቶች ተግባራዊ የሆኑ የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ያካትታል)።
3. የተማሪን ባህሪ ለመገንዘብ የሚያስችሉ ሁኔታውን አስረጂ ባህላዊ ወይም የቋንቋ ምክንያቶች።
4. በክስተቱ አካባቢ የነበሩ ሁኔታዎች።
5. ለአደጋ/ለጉዳት የሚዳርጉ አይቀሬ/አሳሳቢ የሆኑ
6. በቦርድ ፖሊሲ ACA ውስጥ በተገለጹት ግላዊ ባህሪያት ላይ ተሞርኩዞ ቋንቋን ወይም ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን በማሳየት ማንጓጠጥ ወይም የመሳሰሉ ሌሎች የማለዘብ ወይም የማባባስ ሁኔታዎች፣ ከአድሎአዊነት የነፃ፣ እኩልነት እና ባህላዊ ብቃት በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎልን ያስከትላል ተብሎ የሚገመት የዘር ስድብን ጨምሮ። ሆኖም፥ ይህ ክልከላ እንደዚህ ዓይነቱን ቋንቋ፣ ምስሎች ወይም ምልክቶችን ኃላፊነት ባለው መልኩ ለትምህርት ዓላማዎች ውይይት እንዳይውል ለመከላከል ጥቅም ላይ አይውልም።

ተገቢ ያልሆነ ቋንቋን መጠቀም ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት እንዲሁ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት፣ ወይም የንብረት መውደም በሚያስከትሉ ክስተቶች ውስጥ መሣተፍ የዲሲፕሊን እርምጃውን ደረጃ ከፍ የሚያደርጉ ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ።

[2] በስቴት ህግ መሰረት፣ የቅድመ መዋዕለ-ህፃናት ተማሪዎችን እንቅስቃሴ መገደብ እና ማባረር ላይ ከፍተኛ ገደቦች ይኖራሉ። ርእሰ መምህራን/ተወካዮች ለሌሎች ተማሪዎች ወይም ሠራተኞች በሌላ አይነት ማስተካከያ እና ድጋፍ በመስጠት ጉዳቱን ለመቀነስ ወይም ለመከላከል የማያስችል አይቀሬ ከባድ ጉዳት የሚያስከትል ዛቻ/ስጋት መኖሩን ለመወሰን የት/ቤት የስነልቦና ባለሙያ ወይም ሌላ የአእምሮ ጤና ባለሙያ ማማከር አለባቸው። ለጊዜው መታገዱ እንዲቀጥል የትምህርት ቤቱ ርእሰ መምህር/ተወካይ ከወሰነ(ች) ለማፅደቅ፣ ርእሰ መምህሩ/ተወካዩ አግባብ ያለውን የትምህርት፣ ስኬት እና አስተዳደር ዳይሬክተር ማነጋገር አለባቸው። የእገዳ ጊዜ ርዝመት ከአምስት የትምህርት ቀናት መብለጥ የለበትም። ማባረር በፌዴራል ሕግ ድንጋጌ መሠረት በሁኔታዎች የተገደበ ነው። MCPS ደንብ JGA-RB፣ ስለ እገዳ እና መባረርይመልከቱ።

## የባህሪ ማስተካከያ ምላሾች

MCPS ማስተማርን እና መማርን ለመደገፍ ቀጣይነት ያላቸው ትምህርታዊ ስልቶችን እና የባህሪ ማስተካከያ ምላሾችን ይጠቀማል።

የሚቀጥሉት ገፆች እንደሚከተለው ለተለያዩ የዲሲፕሊን ግድፈቶች የት/ቤት ህግ መጣስ/ የግብረመልስ ደረጃዎችን ያስቀምጣሉ፡-

1. የባህሪ ማስተካከያዎች
2. የግብረመልስ ደረጃዎች
3. የባህሪ ማስተካከያ ምንጭ/ሜትሪክስ (Behavior Intervention Matrix)

## በቀጣይነት ትምህርት የማግኘት መብቶች

ከክፍል መቅረቶች ምክንያት የባህሪ ማስተካከያ በፈቃድ መቅረቶች ይሆናሉ።የሜሪላንድ ህግ ከት/ቤት ለተወሰነ ጊዜ የታገዱ ወይም የተሰናበቱ ተማሪዎች እኩል መራመድ እንዲያስችላቸው በተቻለ መጠን በሚከተለው አኳኋን የክፍል ስራ የመስራትና የመከታተል እድል እንዲሰጣቸው ይጠይቃል፡-

1. ከት/ቤት እገዳ የተደረገበ(ባ)ት ወይም የተባረረ(ች) እያንዳንዱ ተማሪ በአማራጭ ትምህርት ፕሮግራም ያልተመደበ(ች) ከሆነ በየቀኑ የክፍል ሥራ እና የትምህርት ስራዎችን በየሣምንቱ ታይቶ ታርሞ ለተማሪው(ዋ) የሚመለስከ ስራ ከእያንዳንዱ መምህር መሰጠት አለበት።
2. እያንዳንዱ ርእሰመምህር ከትምህርት ቤት እገዳ ለተደረገ ባቸው ወይም ለተባረሩ ተማሪዎች እና በመምህራንና በተለያዩ ተማሪዎች መካከል አገናኝ ሠራተኛ (liaison) እንዲኖር ይመድባል።ከዚያም ባሻገር በየሳምንቱ በክፍል እንዲሠሩ የሚሰ ጣቸውን ሥራ እና ከትምህርት ቤት ጋር የተዛመዱ ጉዳዮችን በስልክ ወይም በኢሜል ውጭ ላሉት ተማሪዎች እና ለወላጆ ቻቸው/ለአሳዳጊዎቻቸው በአገናኝ ሠራተኛ (liaison) አማካ ይነት እንዲደርሳቸው ያደርጋል-ታደርጋለች።
3. የአጭር ጊዜ እገዳዎች (እስከ ሶስት ቀናት) የሚቀበሉ ተማሪዎች በእገዳ ወቅት ያመለጡትን የትምህርት ሥራዎች ያለ ቅጣት የማጠናቀቅ ዕድል ይኖራቸዋል። ትምህርት ቤቶች የአጭር ጊዜ እገዳ ለተደረገባቸው እና ለወላጆቻቸው/ለአሳዳጊዎ ቻቸው ይህ መስፈርት መሟላቱን የማረጋገጥ ኃላፊነት ስላለው ሠራተኛ የግንኙነት መረጃ ይሰጣቸዋል።የታገደ/የታገደች ተማሪን ያመለጠውን/ያመለጣትን ስራዎችን የመቀበል፣ ያመለ ጠውን/ያመለጣትን ስራዎችን የመፈጸም እና ፈተናዎችን የማካካስ ሂደት ሌሎቹ ገፅታዎች በማንኛውም በሌላ ጊዜ በምክ ንያት መቅረት ወቅት ስለማካካስ ስራ በያንዳንዱ ት/ቤት በተመ ሰረተው መመርያና ልምድ ጋር ተመሳሳይ ይሆናሉ።

## ከተራዘሙ እገዳዎችና ስንብቶች ጋር የተያያዙ ወቅታዊነት ሁኔታዎች

ከ10 ቀናት በላይ የተማሪዎችን እገዳ ወይም መባረር የጊዜ ገደብ በሚመለከት መከተል የሚያስፈልገውን አሠራር/ህግ የሜሪላንድ ህግ ይደነግጋል። MCPS እነዚህን የጊዜ ማእቀፎች MCPS ደንብ JGA-RB፣ መታገድ እና መባረር እና MCPS ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኛ ተማሪዎችን ማገድ እና ማባረር ላይ ተገልጿል።

MCPS  አንድን ተማሪ በዲስፕሊን ምክንያት ወደ ሌላ ት/ቤት የመመደብ ወይም ወደ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም የመመለስ መብት እና ስልጣን አለው ። አንድ ተማሪ በዲሲፕሊን ምክንያቶች ወደ አማራጭ የትምህርት ፕሮግራም ከተላከ/ከተላከች፣ በMCPS ደንብ JGA-RC የአካል ጉዳተኝነት ያላቸው ተማሪዎች እገዳ ወይም ስንብት "Suspension and Expulsion of Students with Disabilities"በሌላ ካልተገለፀ በስተቀር እንደ ጊዜው አረዛዘም "የተራዘመ እገዳ ወይም ስንብት" ተብሎ ይታሰባል።

## የአካል ጉዳት ያላቸው ተማሪዎች እገዳና ስንብት

የፌዴራል ህግ እንዲታገዱ ወይም እንዲሰናበቱ ስለተወሰነባቸው የአካል ጉድለት ያላቸው ተማሪዎች የህጋዊ አፈፃጸም መብቶችን ያስቀምጣል። እነዚህ መብቶች በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ/ MCPS Regulation JGA-RC በስፋት ተዘርዝረዋል። አካል ስንኩል ተማሪዎች እገዳ እና መባረር

ለተጨማሪ መረጃዎች፣እባክዎን በዚህ መለስተኛ መጽሔት የተጠቀሱትን ልዩ ህጎች፣ መመርያዎች፣ እና ደንቦች ያንብቡ። የቦርድ መመርያዎችና የ MCPS ደንቦች በwww. montgomeryschoolsmd.org/departments/policy ይገኛሉ። በተጨማሪ፣ የትምህርት ቤት አስተዳዳሪዎች የእነዚህ ሠነዶች/ዶኩመ ንቶች ቅጂዎች አሏቸው እና በየትምህርት ቤቶቹ የሚድያ ማዕከላትም ይገኛሉ።

# የባህሪ ማስተካከያዎች

| | |
|---|---|
| የስነምግባር ውል/ኮንትራት | አወንታዊ የስነምግባር የእርምት ርምጃዎች፣ ስልቶች፣ እና ድጋፎችን ለመስጠት በት/ቤት ሰራተኞች የተነደፈ መደበኛ እቅድ አማካይነት የተማሪን ተገቢ ያልሆነ ረባሽ ስነምግባር ማረም። |
| ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ/የመገልገያዎች ባለሞያ "School Counselor/ Resource Specialists" ጋር ተገናኙ | በት/ቤት ሰራተኞች አማካይነት ከት/ቤት አማካሪ፣ ከመገልገያዎች (Resource) መምህር፣ የት/ቤት ሳይኮሎጂስት፣ የት/ቤት ማህበራዊ ሰራተኛ ወይም ከተማሪው የቅርብ ግንኙነት ካለው አሰልጣኝ ጋር ተማሪው እንዲገናኝ ይደረጋል። |
| የመማሪያ ክፍልን በተመለከተ ግብረመልሶች | ለአጭር ጊዜ ማስቆም፣ የአስተማሪና-የተማሪ ኮንፈረንስ፣ የማሰላሰል ወንበር፣ አቅጣጫ መቀየር (ለምሳሌ:- ሚና መጫወት)፣ የመቀመጫ ለውጥ ማድረግ፣ ወላጆችን ማነጋገር፣ ክፍል ውስጥ የተሳትፎ ሚና መገደብ፣ ወይም የይቅርታ ደብዳቤ እንዲጽፉ ማድረግና የመሳሰሉትን በመጠቀም ተማሪዎች ስለባህርያቸው እንዲያንጸባርቁ ማድረግ። |
| የማህበረሰብ አገልግሎት | ተማሪዎች ማህበረሰብን በሚጠቅሙ የተለያዩ ስራዎች ላይ እንዲሳተፉ ማድረግ (ለምሳሌ:- ሾርባ በሚዘጋጅበት ወጥቤት ማሰራት፣ በት/ቤት ወይም በሌላም ስፍራ ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙበትን ቦታ ማፅዳት፣ ወይም የአዛውንቶች መጠቀሚያ ቦታ ላይ መርዳት)። |
| የግጭት አፈታት | (በት/ቤት የተመሰረተ ወይም ከውጭ የተቀናበረ) ግጭቶችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችላቸውን ስልቶች በመጠቀም ተማሪዎች ኃላፊነት እንዲወስዱ መርዳት። ተማሪዎች፣ ወላጆች/አሳዳጊዎች፣ መምህራን፣ የት/ቤት ሰራተኞች፣ እና ወይም ርእሰ መምህራን ግጭትና ንዴትን መቆጣጠር፣ በንቃት ማዳመጥ፣ እና ውጤታማ ግንኙነትን የመሳሰሉ ችግሮችን የመፍታት ክህሎቶችና ተክኒኮችን በሚያራምዱ እንቅስቃሴዎች ላይ ይሳተፋሉ። |
| በቁጥጥር ስር መዋል | አንድን ተማሪ ከትምህርት በፊት፣ በምሳ ወቅት፣ በነፃ የእርፍት ጊዜ፣ ከትምህርት በኋላ፣ ወይም በቅዳሜና እሁድ ለተወሰነ ጊዜ በተለየ መማርያ ክፍል እንዲገኝ/እንድትገኝ ማድረግ። ተማሪዎች ከመታገታቸው/በዉስን ቦታ እንዲቆዩ ሲደረግ አስቀድሞ ትምህርት ቤቶች ለወላጆች/ለሞግዚቶች ለማሳወቅ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል። |
| ማሰናበት | ተማሪዉ(ዋ)ን ከተማሪው/ዋ መደበኛ ት/ቤት ለ45 የትምህርት ቀኖች ወይም ከዚያ በላይ ማገድ፣ ለወላጅ/አሳዳጊ ማስታወቂያ ጋር፣ ይህም ሊሆን የሚችለው በሚከተሉት ሁኔታዎች ብቻ:-<br>1. ዋና የትምህርት ቤቶች ሃላፊ ባለስልጣን ተወካይ ተማሪው/ዋ ከት/ቤት እንዲ ድት ገለል ከተወሰነው ጊዜ አስቀድሞ የተመለሰ/ች እንደሆነ በሌሎች ተማሪዎች ወይም በሰራተኞች ላይ ጉዳት ማስከተሉ አይቀሬነቱን ሲያረጋግጥ፣<br>2. የሱፐርኢንተንደንት ተወካይ ተማሪው(ዋ)ን የማግለል ወቅት እጅጉን ማጠር ያለበትን ያህል ጊዜ ይወስናል/ትወስናለች፤ እና<br>3. የተወገደ/ችው ተማሪ በስኬታማ ሁኔታ ወደ መደበኛ የአካዳሚ ፕሮግራሙ ሊመለስ/ልትመለስ ይችል ዘንድ የት/ቤቱ ስርአት ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶች እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ ይሰጠዋል/ይሰጣታል። COMAR 13A.08.01.11(B)(2)(a -c) |
| ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ እና የእርምት እርምጃ እቅድ | ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ /Functional Behavioral Assessment (FBA) (MCPS Form 336-64) ስለተማሪ አግባብነት የሌለው የሚያሰናክል ባህርይ አካሄድን መረጃ/ኢንፎርሜሽን በመሰብሰብ የት/ቤት ሠራተኞች የተማሪን ባህርይ እንዴት ለማረም ወይም ለመግራት የሚያስችሉ አቀራረቦችን ይወስናል። በመቀጠልም ለተማሪው(ዋ) የሚመጥን የስነምግባር ማስተካከያ ዕቅድ (MCPS Form 336-65 በመጠቀም) ለማዳበር መረጃው ጥቅም ላይ ይውላል። FBA በመጠቀም የትምህርት ቤት ሰራተኞች ቡድን እና የተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ ተገቢውን የባህሪ ግቦችን እና ማስተካከያዎችን በማዘጋጀት የችግሩን ባህሪ ለመከላከል እና ምላሽ ለመስጠት ምትክ ወይም አማራጭ ባህሪን ለማስተማር ስልቶችን ያዘጋጃሉ። |
| በት/ቤት-ውስጥ የሚወሰድ እርምጃ | አንድን ተማሪ በት/ቤት ህንፃ ውስጥ ከነሱ መደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ማስወገድ ነገር ግን ተማሪው/ዋ የሚከተሉትን ለማድረግ እድሎች አሉ(ሏ)ት—<br>(i) በአጠቃላይ ስርአተ ትምህርት በአግባቡ እንዲካሄድ፤<br>(ii) ተማሪው/ዋ የአካል ጉዳተኝነት ያለው/ያላት ተማሪ ከሆነ/ች በህጉ መሰረት በተማሪው/ዋ IEP እንደተወሰነው ልዩ ትምህርትና የተዛመዱ አገልግሎቶች መቀበል፤<br>(iii) በመደበኛ የትምህርት ክፍል ሊያገኝ ከሚገባው/ልታገኝ ከሚገባት ጋር ተመጣጣኝ የሆነ ትምህርት መቀበል፤ እና<br>(iv) ተገቢ እስከሆነ ድረስ ከእኩዮች ጋር በወቅታዊ የትምህርት ፕሮግራማቸው መሳተፍ። COMAR 13A.08.01.11(C)(2)(a) |
| የአሰልጣኝ ፕሮግራም | (ት/ቤትን መሠረት ያደረገ መደበኛ ያልሆነ እና/ወይም የመከላከል እርምጃ) ተማሪዎችን በግል ምክርና ስልጠና የሚሰጡ (ለምሳሌ:- ካውንስለር፣ መምህር፣ የሥራ ባልደረባ፣ አብሮ ተማሪ፣ ወይም የማህበረሰብ አባል) የግል፣ አካደሚክ እና ማህበራዊ እድገታቸውን በመምራት የሚረዱ ሰዎች ጋር ማቀናጀት። |

# የባህሪ ማስተካከያዎች (የቀጠለ)

| | |
|---|---|
| ወላጅን መድረስ | የልጆቻቸውን ባህሪ ለወላጆች/አሳዳጊዎች ማሳወቅ እና በስነስርዓት አውድ ውስጥ ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪን ለማረም የእነሱን እርዳታ መፈለግ። |
| የወላጅ/አሳዳጊ እና የተማሪ/መምህር ስብሰባ | ተማሪዎችን፣ ወላጅ/አሳዳጊዎችን፣ መምህራንን፣ የት/ቤት ሰራተኞችን፣ እና/ወይም ርእሰመምህራንን ስለ ተማሪዎች ማህበራዊ፣ አካደሚያዊ፣ እና ከስነምግባር ጋር የተያያዙ የግል ጉዳዮችን በሚመለከቱ አይነተኛ የስነምግባር መፍትሄዎች ውይይቶች ማሳተፍ። |
| የእኩያ ግልግል/ሽምግልና | ስልጠና ያገኙ ተማሪዎች እንደ ገላጋይ/ሽማግሌ የሚያገለግሉበትና እኩዮቻቸው ግጭቶችን እንዲቋቋሙና መፍትሄዎችን በማዳበር እንዲያግዟቸው የሚደረግበት የግጭት መፍቻ ዘዴ ተግባራዊ ማድረግ። |
| ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድ ማቅረብ | ለረዥም ጊዜ እንዲታገድ/እንድትታገድ፣ እንዲወገድ/እንድትወገድ፣ ወደ አማራጭ የማስተማር ዘይቤ፣ ወይም  ወደ ህግ አስከባሪ እንዲተላለፍ (እንድትተላለፍ) ለት/ቤት አስተዳደር (አስተዳዳሪዎች) ስለ ተማሪ አስተያየት መስጠት፣ |
| ወደ አማራጭ ትምህርት ማስተላለፍ | ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation IOI-RA ጋር በሚጣጣም መልኩ ተማሪ ወደ አማራጭ ፕሮግራም እንዲዛወር/እንድትዛወር ለት/ቤት አስተዳደር (አስተዳዳሪዎች) አስተያየት መስጠት፣ ለአማራጭ ፕሮግራሞች የምደባ ሂደት/አፈጻጸም። |
| እፆችን ያለአግባብ ስለመጠቀም/መጥፎ አጠቃቀም (Substance Abuse) ማስተላለፍ የምክር አገልግሎቶች | ከርእሰ መምህር/ት ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር፣ ወደ አካባቢ የጤና መምርያ ወይም ማህበረሰብን መሰረት ላደረገ አገልግሎት ከመጥፎ የዕፅ አጠቃቀም ጋር ለተያያዘ የምክር አገግሎት በት/ቤት ውስጥም ሆነ ከት/ቤት ውጭ አገልገሎቶች ወደሚሰጡበት ተማሪዎችን መምራት። |
| ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅት መምራት/ማስተላለፍ | ከ ርእሰመምህር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር ከትምህርት ሠዓት በኋላ-ፕሮግራም፣ የግል ወይም የቡድን የምክር አገልግሎት፣ የአመራር እድገት፣ ግጭቶችን ማስታረቅ፣ እና/ወይም ግላዊ ስልጠና ወደሚያካትቱ የተለያዩ አገልግሎቶች ተማሪዎችን መምራት። |
| ወደ ጤና/ የአእምሮ ጤና አገለግሎቶች መምራት | ከ ርእሰመምህር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር፣  ምክርና ግምገማ እንዲደረግላቸው የሚያስፈልጋቸው ተማሪዎችን በት/ቤት የተመሰረቱ ወይም በማህበረሰብ ወደ ተመሰረቱ የጤና እና የአእምሮ ጤና ክሊኒኮች ወይም ሌሎች አገልገሎቶች መምራት/መላክ። ተማሪዎች ተገቢ ወዳልሆኑ ወይም ረብሸኛ ስነምግባሮች ወይም በትምህርታቸው ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያደርጉ አሳሳቢ ጉዳዮቻቸውን ከሌሎች ገንቢ ምክር ለማግኘት በግል እንዲያጋሩ እና በግል የሚፈታተኗቸውን ነገሮች ለመቋቋም የሚያግዙዋቸውን ቴክኒኮች እንዲማሩ ይበረታታሉ። እነዚህ አገልግሎቶቸች ቁጣ/ንዴትን-መቆጣጠር (anger-management) ትምህርቶች እና በግላጭ ወይም ግልፅ ያልሆነ የግል ስልጠና ሊያካትቱ ይችላሉ። |
| ወደ ተማሪ መምራት የድጋፍ ቡድን | ከ ርእሰመምህር ወይም ተወካይ ጋር በመመካከር፣ የተማሪን ውጤት ለማሻሻል የመከላከያና የእርምት ቴክኒኮችና አማራጭ ስልቶችን ለማዳበር የት/ቤት አማካሪዎች፣ የተማሪ ፐርሶኔል ሰራተኞች፣ መምህራን፣ ርእሰመምህራን፣ የማህበራዊ አገልግሎት ሰራተኞች (social workers)፣ የጤና አገልግሎቶች፣ የጤና ክሊኒክ ሰራተኞች፣ የት/ቤት ሳይኮሊጂስቶች፣ እና የውጭ ተቋም ተወካዮችን ሊያጠቃልል የሚችል የድጋፍ ቡድን የተማሪውን ጉዳይ ከሚከታተለው ሰው (case manager) ስር ማሰባሰብ። የተማሪ ድጋፍ ቡድን ባዘጋጀው እቅድ አፈጻጸም የተማሪ ባህርይ/ስነምግባር ካልተሻሻለ፣ ቡድኑ ከሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ/MCPS Regulation IOI-RA፣ ጋር በተጣጣመ መልኩ የምደባ አማራጭ ይጠይቃል፣ ለአማራጭ ፕሮግራሞች የምደባ ሂደት። |
| ከትምህርት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች መወገድ /የጥቅሞች መብት ማጣት"Extracurricular Activities" | ከ ርእሰ መምህር ወይም ተወካይ ጋር በመነጋገር፣ ተማሪ ከከሪኩለም ትምህርት ተጨማሪ እንቅስቃሴዎች ላይ የመሳተፍን መብት ለመንፈግ/፣ ስፖርት እና ክለቦችን፣ ወይም ተማሪ በት/ቤት ሁነቶች ላይ ወይም እንቅስቃሴዎች (እንደ መስክ ጉዞ ወይም በት/ቤት ዳንስ መሳተፍን የመሳሰሉ) ላይ እንዳይሳተፍ/እንዳትሳተፍ ማገድ። ስነ ምግባሩ የዚህን አይነት ምላሽ አስገዳጅ ካደረገው፣ለጎደለው እንቅስቃሴ በተማሪው(ዋ) የተከፈሉ ገንዘቦች ካሉ፣ከተቻለ፣ መመለስ አለባቸው። |
| ወደ ቦታው መመለስ/ካሳ | በተማሪው(ዋ) ስነምግባር ምክንያት በሌሎች ላይ ለደረሰ ጥፋት፣ ብልሽት፣ ወይም ጉዳት ተማሪው እንዲክስ መጠየቅ። ካሳው በገንዘብ ወይም ተማሪውን(ተማሪዋን)  በት/ቤት ፕሮጀክት ስራ እንዲሰራ በመመደብ፣ ወይም በሁለቱም ሊከናወን ይችላል።<br><br>COMAR 13A.08.01.11(D) ድንጋጌ መሰረት አንድ ተማሪ የስቴት ወይም የአካባቢ ህግን ወይም መመሪያን ከጣሰ(ች) እና ጥሰቱ በተፈጸመበት ጊዜ ወይም ምክንያት የትምህርት ቤቱን ንብረት ጉዳት ከደረሰበት ወይም ንብረት ዋጋው በእጅጉ ከቀነሰ። ወይም በወቅቱ በትምህርት ቤት ንብረት ላይ የነበረ የሌላ ሰው ንብረት ላይ ጉዳት ከደረሰ፣ ርእሰ መምህሩ ከተማሪው(ዋ) ወላጅ/አሳዳጊ እና ሌሎች አግባብነት ካላቸው ግለሰቦች ጋር በጉዳዩ ላይ ኮንፈረንስ ካደረጉ በኋላ እንዲመልሱ ይጠይቃሉ።የገንዘብ ካሳ ከ$2,500 ወይም ከንብረቱ የገበያ ዋጋ ግምት ወይም ከሁሉቱ የአነስተኛውን ዋጋ በላይ መሆን የለበትም። |

# የባህሪ ማስተካከያዎች (የቀጠለ)

| | |
|---|---|
| ሁኔታዎችን ማደስ (Restorative) አፈፃጸም | (ክፍል-ተኮር ወይም የተመቻቸ-ስፔሻሊስት) የተሃድሶ ተሞክሮዎች አዎንታዊ የትምህርት ቤት ሁኔታን ለመመስረት እና ለመጠበቅ፥ ተገቢ ማህበራዊ ክህሎቶችን ለማስተማር የተቀናጀ አካሄድ ለመመስረት በንቃት ይጠቀማሉ። የማገገሚያ ተሞክሮዎች በአንድ ሰው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለመለየት እና ለመቅረፍ የተነደፉ ማስተካከያዎችን፣ እናም ጉዳቱ ለደረሰበ(ባ)ት ተማሪ ሁኔታውን ለመፈወስ እና ለማረም እቅድ ለማውጣት ልምዶችን ይጠቀማሉ። የበለጠ መረጃ ለማግኘት MCPS Regulation JGA-RB፣ እገዳ እና ማባረርይመልከቱ ። |
| በት/ቤት-የተመሰረተ ወይም የማህበረሰብ ስብሰባ | ተማሪዎችን፣ የት/ቤት ሰራተኞችን እና በግጭቱ የተሳተፉ ሌሎችን በርእሱ ለመወያየት፣ ጉዳዮችን ለመፍታት፣ እና መፍትሄዎች ለማቅረብ መሰብሰብ (ለምሳሌ፡- “Daily Rap,” “Morning Meetings”)። |
| እገዳ (ለአጭር ጊዜ ከት/ቤት ውጭ ማቆየት) | በርእሰመምህር አንድን ተማሪ በዲሲፕሊን ምክንያት እስከ ሶስት ቀን፣ ነገር ግን ከሱ ሳይበዛ፣ ከት/ቤት ማስወገድ፣ (ለወላጅ/ለአስዳጊ ከማሳወቅ ጋር) |
| እገዳ (ለረጅም ጊዜ፣ ከት/ቤት ውጭ) | ለወላጅ/አሳዳጊ እያስታወቁ፣ በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያቶች የአንድ ተማሪ ከት/ቤት ከ4 እስከ 10 የትምህርት ቀኖች በርእሰመምህሩ/ሯ መታገድ። |
| እገዳ (በት/ቤት ውስጥ) | ለወላጅ/አሳዳጊ እያስታወቁ፣ በዲሲፕሊን ጉድለት ምክንያቶች የአንድ ተማሪ በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከወቅታዊ የት/ቤት ፕሮግራም እስከ 10 ቀናት፣ ነገር ግን ከዚያ ለማይበልጡ ቀኖች በት/ቤቱ ርእሰመምህር መታገድ። |
| እገዳ (ለረጅም ጊዜ ከት/ቤት ውጭ ማቆየት) | ለወላጅ/አሳዳጊ በማሳወቅ ተማሪን ከት/ቤት መደበኛ ፕሮግራም ለተራዘመ ጊዜ ( ከ11 እስከ 45 የትምህርት ቀናት) ማገድ፣ በሚከተሉት ሁኔታዎች ምክንያት ብቻ ሊደረግ ይችላል፡-<br>1. የሱፐርኢንተንደንት ተወካይ የሚከተሉትን ሲያረጋግጥ፡-<br>ሀ/ የተወሰነው የእገዳ ጊዜ ከመፈፀሙ በፊት የተማሪው/ዋ ወደ ት/ቤት መመለስ በሌሎች ተማሪዎችና ሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ፤ ወይም<br>ለ. ተማሪው/ዋ ያደረገው/ችው ተደጋጋሚና ከፍተኛ ረብሻ በሌሎች ተማሪዎች የትምህርት ሂደት ላይ መጠነ ሰፊ እክል በሙሉ የትምህርት ቀን ላይ ፈጥሯል፣ እንዲሁም ሌሎች መተግበር የሚቻሉ እና ተገቢ የስነምግባርና የዲሲፕሊን ማስተካከያዎች በሙሉ ተሞክረዋል።<br>2. የትምህርት ቤቶች ሱፐርኢንተንደንት ተወካይ የእገዳውን ወቅት እጅጉን ሊያጥር ወደሚችልበት ጊዜ ይቀንሳል።<br>3. የተማሪው(ዋ)ን ወደ መደበኛ አካዴሚያዊ ፕሮግራም በስኬት እንዲመለስ/እንድትመለስ ለማድረግ ት/ቤቱ ለተወገደ(ች)ው ተማሪ ተመጣጣኝ የትምህርት አገልግሎቶች እና ተገቢ የስነምግባር ድጋፍ ያቀርብለ(ላ)ታል። |
| ከመማርያ ክፍል በጊዚያዊነት መወገድ | ተማሪዎችን በት/ቤት ቅጥር ግቢ ውስጥ ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራማቸው ለአንድ፣ ነገር ግን ከዚያ ለማይበልጥ፣ የትምህርት ፔርየድ ማገድ። |

# የግብረመልስ ደረጃዎች

መዘዞች የግለሰባዊ ሁኔታዎችን ለመቅረፍ ሊዘጋጁ ይችላሉ፥ ስለዚህ ከአንድ በላይ በሆነ ደረጃ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ይሆናሉ።

<table>
<tr><td rowspan="3">ደረጃ 1</td><td colspan="2">በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ እርምት ምሳሌዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">እነዚህ የእርምት ርምጃዎች የተተለሙት ለተማሪዎች አክብሮትን አውቀው ለሰላማዊ አካባቢ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ አግባብ ያለው ስነምግባር ለማስተማር ነው። መምህራን የተለያዩ የማስተማርና መማርያ ክፍልን የመምራት ስልቶችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይበረታታሉ። ተገቢ በሚሆንበት ጊዜ፣ መምህራን የተማሪው(ዋ)ን የመማር እና የባህሪ ለውጥ ወጥነት ለማረጋገጥ ለተማሪው(ዋ) ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ አስተዋፅዖ የሚያደርጉትን ሁኔታዎች ለማስተካከል የድጋፍ ሥርዓት ስኬታማ እንዲሆን በሚደረገው እንቅስቃሴ መሳተፍ ይችላሉ። እነዚህ የስነምግባር እርምቶች በስራ ላይ የሚውሉት ደረጃ በደረጃ መሆን አለበት።</td></tr>
<tr><td>• በመማርያ ክፍል- የተመሰረቱ ርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የቃል እርምት፣ በፅሁፍ ይቅርታ፣ ማስታወስ/ሌላ እቅጣጫ መቀየስ፣ ገፀ-ባህርይ መስራት፣ እለታዊ የክንውን ማስታወሻ)<br>• በቁጥጥር ስር ማዋል<br>• የማገገሚያ ተግባሮች (በመማርያ ክፍል የተመሰረቱ)<br>• የእኩያዎች የእርቅ ሽምግልና<br>• ት/ቤትን መሠረት ያደረገ ግጭት የማስወገድ መፍትሄ</td><td>• ት/ቤትን መሠረት ያደረገ ስብሰባ<br>• ወላጅን/ሞግዚትን ለመድረስ (ወላጅ/አሳዳጊን በስልክ፣ በኢሜል ወይም በጽሑፍ ማግኘት ይቻላል)<br>• ይፋ ያልሆነ እና/ወይም ት/ቤትን መሠረት ያደረገ የመከላከል ምክር/ክትትል ማድረግ<br>• ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ/የመገልገያ ባለሙያዎች ክትትል ማድረግ</td></tr>
<tr><td rowspan="3">2ኛ ደረጃ</td><td colspan="2">በመምህር-የሚመሩ/በአስተዳደር የተፈቀዱ የእርምት ምሳሌዎች</td></tr>
<tr><td colspan="2">እነዚህ የእርምት ርምጃዎች የተተለሙት ተማሪዎች አክብሮትን አውቀው ለሰላማዊ አካባቢ አስተዋፅኦ እንዲያደርጉ ተገቢ ስነምግባር ለማስተማር ነው። ከነዚህ አብዛኛዎቹ እርምት ርምጃዎች የተማሪውን/የተማሪዋን የስነምግባር ማሻሻል ድጋፍ ዘዴዎችን በማዋሃድ እና ለተማሪው/ዋ ተገቢ ያልሆነ ወይም ረብሸኛ ስነምግባር አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ለመለወጥ የተተለሙ ናቸው። እነዚህ ግብረመልሶች፣ ባንድ በኩል ተማሪውን/ተማሪዋን ከት/ቤት እንዳይለይ እየተደረገ፣ በጉዳዩ አስከፊነት ላይ በማተኮር እና ወደፊት ሊያደርስ የሚችለውን ከፍተኛ ጉዳት አስተዋጽኦ በመግለፅ ስነምግባርን የማረም አላማ አላቸው። እነዚህ ግብረመልሶች አገልግሎት ላይ የሚውሉት ደረጃ በደረጃ መሆን አለበት። ለማንኛውም የተማሪዎችን ጤንነት ወይም ደህንነት ሊጎዳ ለሚችል ከባድ ክስተት ከአስተማሪ ወደ አስተዳደራዊ እርምጃ የመምራት ድጋፍ ያስፈልጋል።</td></tr>
<tr><td>በመምህር-የሚመራ<br>በመማርያ ክፍል ደረጃ ሊከናወን ይችላል<br>• በትምህርት ክፍል ውስጥ የተመሰረቱ እርምቶች (ለምሳሌ፣ የቃል እርምት፣ የፅሁፍ ይቅርታ፣ ማስታወስ/ሌላ አቅጣጫ መቀየስ፣ ገፀ-ባህርይ መጫወት/መስራት፣ እለታዊ ክንውን መመዝገብ)<br>• የስነምግባር ስምምነት<br>• ወላጅን/ሞግዚትን ለመድረስ (ወላጅ/አሳዳጊን በስልክ፣ በኢሜል ወይም በጽሑፍ ማግኘት ይቻላል)<br>• ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ/የመገልገያ ባለሙያዎች ክትትል ማድረግ<br>• ቁጥጥር ስር ማድረግ<br>• ከመማርያ ክፍል በጊዜያዊነት ማስወገድ<br>• የወላጅ/አሳዳጊ እና የተማሪ ስብሰባ (ከመምህር ጋር)<br>• ይፋ ያልሆነ እና/ወይም በት/ቤት የተመሰረተ የመከላከል ተመክሮ መስጠት<br>• የተሐድሶ ተሞክሮዎች (በመማሪያ ክፍል-ተኮር ወይም በፍትሃዊ ተሃድሶ አሠልጣኝ፣ በልዩ ባለሙያ ወይም በትምህርት ቤት አስተዳዳሪ የሚመቻቹ)</td><td>ከአስተማሪ የተመራ<br>ከአስተዳደር ድጋፍ ጋር የተከናወነ<br>• ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ/የስነምግባር ማስተካከያ እቅድ<br>• የአደንዛዥ እፅ አላግባብ መጠቀምን ለተገቢው የካውንስሊንግ አገልግሎት ማስተላለፍ<br>• ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅት መምራት/ማስተላለፍ<br>• ወደ ጤና/የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች መምራት/ማስተላለፍ<br>• የተሐድሶ ተሞክሮዎች (ክፍል-ተኮር ወይም ፍትሃዊ ተሃድሶ አሠልጣኝ፣ በልዩ ባለሙያ ወይም በትምህርት ቤት አስተዳዳሪ የተመቻቸ)<br>• ልዩ የተሳትፎ መብቶችን ማጣት/ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች መወገድ<br>• ወደ ቦታው መመለስ/ካሳ<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት<br>• በት/ቤት የተመሰረተ ወይም በውጭ የተካሄደ የግጭት መፍትሄ<br>• በት/ቤት የሚካሄድ ወይም የማህበረሰብ ስብሰባ<br>• በእኩዮች የሚደረግ የእርቅ ሽምግልና<br>• ወደ ተማሪ ድጋፍ ቡድን ማስተላለፍ</td></tr>
</table>

## ምላሽ የሚሰጥባቸው ደረጃዎች (ተከታታይ)

| | |
|---|---|
| | **በአስተዳደር የተደገፉ እና ወይም የማስወገድ አፃፉ/ምላሽ ምሳሌዎች** |
| **3ኛ ደረጃ** | እነዚህ አፃፉዎች ስኬታማ መማርን ለማረጋገጥና እና ለተማሪው/ዋ ተገቢ ያልሆነ ወይም ረብሸኛ ስነምግባር አስተዋፅኦ የሚያደርጉ ሁኔታዎችን ለመለወጥ ያገለግላሉ። የእነዚህ እርምቶች ዓላማ፡- ባንድ በኩል ተማሪውን/ተማሪዋን ከት/ቤት እንዳይርቅ/እንዲቆይ እያደረጉ፣ ነገር ግን ያደረሰው/ችው ጥፋት ላይ በማተኮር እና ወደፊት ሊያደርስ የሚችለውን ከባድ ጉዳት በመግለፅ ስነምግባርን የማረም አላማ አላቸው። እነዚህ እርምቶች በት/ቤት-ውጥ ከክፍል ማገድ ወይም በት/ቤት ውስጥ የማስተካከያ ክትትልን ሊያካትቱ ይችላሉ። ለስነምግባር ርምጃ ተገቢ ምላሽ የመስጠት ብቃቱ ቸል ሳይባል የዚህ አይነቱ እገዳ በተቻለ መጠን መቀነስ አለበት።  እነዚህ የእርምት ርምጃዎች በተግባር ላይ መዋል ያለባቸው ደረጃ በደረጃ ከአስተዳደር ድጋፍ ጋር መሆን አለበት።<br><br>• በትምህርት ክፍል ውስጥ የሚወሰዱ የእርምት ርምጃዎች(ለምሳሌ፣ የቃል እርምት፣ በፅሁፍ መግለጥ/ይቅርታ፣ ማስታወሻ/ሌላ አቅጣጫ መምራት፣ ገፀ ባህርይ-መስራት፣ የእለታዊ ክንዋኔ ማስታወሻ)<br>• የስነምግባር ስምምነት<br>• የማህበረሰብ አገልግሎት<br>• የወላጅ/አሳዳጊ እና የ ተማሪ ስብሰባ (ከአስተዳዳሪ ጋር)<br>• ይፋ ያልሆነ/መከላከያ/ይፋ ስልጠና/ማማከር<br>• ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ድርጅት መምራት/ማስተላለፍ<br>• ወደ ተማሪ ድጋፍ ቡድን ማስተላለፍ<br>• ቁጥጥር ስር ማድረግ<br>• ከትምህርት ክፍል በጊዚያዊነት መወገድ<br>• ት/ቤት ውስጥ መታገድ<br>• ት/ቤት ውስጥ የማስተካከያ ክትትል<br>• የማህበረሰብ መሰባሰብ<br>• ተግባርዊ የስነምግባር ግምገማ/የስነምግባር ማስተካከያ እቅድ<br>• በት/ቤት ወይም በውጭ የተስተናገደ ግጭት መፍታት<br>• ሱስ የሚያስይዙ ነገሮችን በአግባብ አለመጠቀም ለምክር አገልግሎቶች ማስተላለፍ<br>• ወደ ጤና/የአእምሮ ጤና አገልግሎቶች መላክ/ማስተላለፍ<br>• የተሐድሶ ተግባሮች (በመማርያ ክፍል የተመሰረተ ወይም በባለሙያ የሚሰጥ)<br>• ልዩ የተሳትፎ መብቶችን ማጣት/ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች መወገድ<br>• ወደ ቦታው መመለስ/ካሳ |
| | **የአስተዳደራዊ ድጋፍና ለአጭር ጊዜ ከት/ቤት ውጭ የማግለል እርምጃ ምሳሌዎች** |
| **4ኛ ደረጃ** | እነዚህ የእርምት ርምጃዎች ተማሪው/ዋ ት/ቤት ውስጥ እያለ/ች አሳሳቢ የስነምግባር ጉድለቶችን ማረምን ይመለከታሉ። ሲያስፈልግ፣ እንደ ስነምግባሩ ሁኔታ ሆነ ወይም ለወደፊት ለሚደርስ ከፍተኛ ጉዳት ምክንያት፣ ተማሪው/ዋ ከት/ቤቱ አካባቢ ሊወገድ/ልትወገድ ይችላል/ትችላለች።እነዚህ ምላሾች ራስን የማጥፋት እና አደገኛ ባህሪን በመቅረፍ የትምህርት ቤትን ማህበረሰብ ደህንነት ያበረታታሉ እናም በአስተዳደራዊ ድጋፍ ቀስ በቀስ - ደረጃ በደረጃ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።<br><br>• የወላጅ/አሳዳጊ እና የተማሪ ስብሰባ (ከአስተዳዳሪ ጋር)<br>• ልዩ የተሳትፎ መብቶችን ማጣት/ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች መወገድ<br>• ወደ ቦታው መመለስ/ካሳ<br>• በት/ቤት ውስጥ መታገድ<br>• ተግባራዊ የስነምግባር ግምገማ/የስነምግባር ማስተካከያ እቅድ<br>• ይፋ የማማከር/ማሰልጠን/ማበረታታት ዕቅድ<br>• የአጭር ጊዜ ከት/ቤት ውጭ እገዳ (1-3 ቀኖች)<br>• የማገገም ድርጊቶች (በመማርያ ክፍል የተመሰረተ ወይም በባለሙያ የሚስተናገድ) |
| | **በአስተዳደራዊ ውሳኔና ድጋፍ ለረጅም ጊዜ ከት/ቤት ውጭ የማግለል እና ሪፈራል ምላሽ ምሳሌዎች** |
| **ደረጃ 5** | እነዚህ የእርምት ርምጃዎች በስነምግባሩ ከባድነትና ለወደፊት ያስከትላል ተብሎ የሚገመት ከባድ ጉዳት ምክንያት አንድን ተማሪ ከት/ቤት አካባቢ ለተራዘመ ጊዜ ማስወገድ። ተማሪው/ዋ/ን ተጨማሪ የተደራጀ መዋቅርና አገልግሎቶች ባሉበት በደህና አካባቢ ማቆየትን ሊያካትት ይችላል። እነዚህ ምላሾች ለራስ መሰናክል የመሆን እና አደገኛ ባህሪን በማሻሻል የትምህርት ቤትን ማህበረሰብ ደህንነት ያበረታታሉ፥ እናም በአስተዳደራዊ ውሳኔና-ድጋፍ ጥቅም ላይ መዋል አለባቸው።<br><br>• የማቅናት/የማገገም ተግባር (በመማርያ ክፍል የተመሰረተ ወይም በባለሙያ የሚስተናገድ)<br>• ተጨማሪ እርምጃ እንዲወሰድ ማስተላለፍ<br>• ወደ አማራጭ ትምህርት መምራት<br>• ወደ ተማሪ የድጋፍ ቡድን መምራት<br>• ወደ ቦታው መመለስ/ካሳ<br>• ልዩ የተሳትፎ መብቶችን ማጣት/ከትምህርት ውጭ እንቅስቃሴዎች መወገድ<br>• ከት/ቤት ውጭ እገዳ<br>  ◦ ረጅም ጊዜ (4-10 ቀኖች)<br>  ◦ የተራዘመ (11-44 ቀኖች)<br>• ማባረር (ከመደበኛ የትምህርት ፕሮግራም ለ 45 ቀናት ወይም ለሚበልጥ ጊዜ ማስወገድ) |

# የባህሪ ማስተካከያ ሜትሪክስ

ይሄ የባህሪ ማስተካከያ ሜትሪክስ (Matrix) መሰረት ያደረገው የሜሪላንድ ስቴት የትምህርት ቦርድ የስነምግባር ህግን ነው። MCPS የባህሪ ማስተካከያ፣ የደህንነት እና ጤናማነት ፍልስፍና እና ወቅታዊ ትግበራ እንዲሁም ከሚመለከታቸው አካላት ከሚሰጥ ግብዓት ጋር ለማቀናጀት የተወሰኑ ክለሳዎች ተደርገዋል። ማትሪክስ/matrix አግባብነት ለሌለው ወይም የሚረብሽ የተማሪ ባህሪን የሚመለከት ተከታታይ ምላሾችን ይሰጣል።የትምህርት ቤት ሰራተኞች አጠቃላይ ሁኔታዎችን ያገናዘበ እና ከዲሲፕሊን ፍልስፍና፣ የቦርድ ፖሊሲዎች፣ MCPS ደንቦች እና ከሚመለከ ታቸው የፌደራል እና የስቴት ህጎች ጋር የሚጣጣሙ የዲሲፕሊን ውሳኔዎችን የማድረግ ኃላፊነት አላቸው። ሜትሪክሱ ሊደርሱ የሚችሉ ተገቢ ያልሆኑ ወይም የመረበሽ ባህሪያትን (በስቴት የተለዩ ከትምህርት እንዲታገድ የማድረግ ኮድ) እና ተገቢ ማስተካከያዎችን ወይም የሚያስከትሉ መዘዞችን/ውጤቶችን ዝርዝር ይዟል።አላማው አምስት የተለያዩ እርከኖች ያሉት የድጋፍ፣ የማስወገጃ፣ እና ለተማ ሪዎች ተገቢ ያልሆኑ ወይም ረብሻ-ነክ ስነምግባሮች አስተዳደራዊ እርምጃ ቀደም ብሎ ከተሰጠው መግለጫ እና ሰንጠረዥ ጋር አብሮ ስራ ላይ እንዲውል ነው።

በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው፣ ከአድሎአዊነት የነፃ፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት፣ አድሎአዊነትን አይታገስም። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስን (MCPS) የሁሉንም ተማሪዎች እና ሰራተኞች ኃላፊነቶቹን የመወጣት እና የማህበረሰባ ችንን የረዥም ጊዜ ጥረት ለማሳካት ፍትሃዊነትን፣ አካታችነትን እና ሁሉንም ሰው የመቀበል ብቃትን ያሰናክላል። ቦርዱ የቋንቋ አጠቃ ቀምን እና/ወይም ምስሎችን እና ምልክቶችን በማሳየት የሚደርግ ጥላቻን እና በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ሊያስከትሉ የሚችሉ ድርጊቶችን ይከለክላል። የጥላቻ ቋንቋን መጠቀም ወይም ጥላቻን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት የመሳሰሉ አንዳንድ ክስተቶች የዲሲፕሊን ምላሽ ደረጃን ከፍ የሚያደርግ ነገር ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል።

በባህሪ ማስተካከያ ሜትሪክሱ ላይ የተገለፁ የባህሪ ማስተካከያ ደረጃዎች በሚከተለው መንገድ ተግባር ላይ መዋል አለባቸው:-

- ተገቢ ላልሆነ ወይም የመረበሽ ባህሪ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ማስተካከያዎች ወይም የባህሪ ማስተካከያዎች በሚመረጡበት ውቅት፣ የት/ቤቱ ሰራተኛ ይሄንን ባህሪ ከሜትሪክሱ ውስጥ መለየት አለበት። ሊደርሱ የሚችሉ ጥሰቶች የተጠቀሱ ምሳሌ ዎችን፣ ነገር ግን በነሱ ሳይወሰን፣ ያካትታል።
- ተገቢ ያልሆነ ወይም የመረበሽ ባህሪ የመጀመርያ ሲሆን፣ የት/ቤት ሰራተኛ መጀመርያ ማገናዘብ ያለበት ከሜትሪክሱ (Matrix) ውስጥ ከሁሉም አነስተኛውን ደረጃ ማስተካከያዎች ወይም የዲሲፕሊን ምላሾች መካከል መሆኑን ነው (አንድ ወይም ከዚያ በላይ የሆኑ ማስተካከያዎች ወይም የዲሲፕሊን እርምጃዎች ከዝቅተኛ ደረጃ መጀመር)።
- በዚያው የትምህርት አመት ተመሳሳይ ባህሪ ከተደጋገመ፣ የት/ቤቱ ሰራተኞች በሜትሪክሱ ላይ ከተመለከቱት የዲስፕሊን እርምጃዎች የሚቀጥለውን ከፍተኛ ደረጃ አንድ ወይም ከዚያ በላይ ማስተካከያዎች ወይም የዲሲፕሊን እርምጃዎችን ለዚያ ባህሪ፣ ወይም ለማንኛውም ዝቅተኛ ደረጃ፣ ተገቢ የባህሪ ማሻሻል ስራዎችን ጨምሮ መጠቀም ሊያስቡ ይገባል።
- ሰራተኛ ተማሪውን ከመማርያ ክፍል ማስወገድን ሊያካትቱ ከሚችሉ ከፍተኛ ደረጃዎች ከመሄዳቸው በፊት በርካታ ዝቅተኛ ደረጃ ማስተካከያዎችን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይበረ ታታሉ።
- ርእሰ መምህራን ልዩ ሁኔታዎች እንዳሉ ወይም በተማሪዎች ወይም በሰራተኞች ላይ ከባድ ጉዳት ሊደርስ እንደሚችል ከገመቱ፣ ከከፍተኛው ደረጃ በላይ ወይም በሜትሪክሱ ላይ ከተጠቀሰው ዝቅተኛ ደረጃ በታች የሆነ ማስተካከያ ወይም የዲሲፕሊን እርምጃ ምላሽ ይሰጣሉ፣ ሆኖም ርዕሰ መምህራን እርምጃ ከመውሰዳቸው በፊት ከአካባቢያቸው በትምህርት ቤት ድጋፍ እና ደህንነት ቢሮ (OSSWB) ተባባሪ ሱፐርኢንተን ደንት ጋር መማከር/ማስፈቀድ አለባቸው።

| ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል) | ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)። ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ደረጃ 1** በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | **ደረጃ 2** በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | **ደረጃ 3** በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | **ደረጃ 4** በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | **ደረጃ 5** የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
| **ክፍል/ትምህርት ማቋረጥ (101)** | ት/ቤት ከደረሱ በኋላ የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር ከክፍል መቅረት።[1፣2] | | | | |
| | ት/ቤት ከደረሱ በኋላ በተከታታይ የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር ከክፍል መቅረት። | | | | |
| **መዘግየት/ማርፈድ (102)** የሚዘገዩ/የሚያረፍዱ የኤሌሜንታሪ ተማሪዎች የከበደ ቅጣት ወይም የማግለል ርምጃ መሰጠት የለባቸውም፣ነገር ግን ወላጆቻቸው/አሳዳጊዎቻቸው እንዲያውቁት መደረግ አለበት። | የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር ወደ ክፍል ወይም ወደ ት/ቤት ከአንድ ጊዜ በላይ ዘግይቶ መድረስ።[1,2] | | | | |
| | ወደ መማርያ ክፍል ወይም ት/ቤት የተፈቀደ ምክንያት ሳይኖር አዘውትሮ ዘግይቶ መድረስ። [1,2] | | | | |
| **ውስልትና/ዋልጌነት (103)** የአንደኛ ደረጃ እና የመካከለኛ ደረጃ ተማሪዎች ሕጋዊም ይሁን ሕጋዊ ባልሆነ ምክንያት በተደጋጋሚ የሚያረፍዱ፣ ወይም የሚቀሩ ከሆነ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ መወሰድ አለበት። በርእሰመምህሩ/ሯ ወይም በእርሱ/ሷ ተወካይ ፈቃድ፣ ደጋግሞ የመቅረት አዝማሚያ ያሳዩ ተማሪዎች በት/ቤት በመደበኛነት መገኘትን ለመጨመር የተቀረጹ ከበድ ያለ የባህሪ ማስተካከያ አገልግሎቶች እንዲያገኙ ለማድረግ ወደ ተገቢው ሠራተኛ ወይም ከት/ቤት ውጭ ወደ ሚገኙ ሌላ ኤጀንሲዎች ሊላኩ ይችላሉ። አምስት ጊዜ ወይም ከዚያ በላይ ያለምክንያት የቀሩ ተማሪዎች ከት/ቤት ትምህርት ላይ ያለመገኘታቸውን የሚገልጽ ደብዳቤ ይሰጣቸዋል። *ይመልከቱ፡- MCPS ደንብ JEA-RA፣ Student Attendance/የተማሪ ክትትል | ባልተፈቀደ ምክንያት ከት/ቤት መቅረት።[1፣2] | | | | |
| | ወስላታ/ዋልጌ መሆን።[3] | | | | |

[1]አንድ ተማሪ "ት/ቤት አለመገኘት ጋር በተያያዙ ጉድለቶች ምክንያት ብቻ" ከት/ቤት ሊታገድ ወይም ከት/ቤት ሊሰናበት አይችልም። MD. ANN. CODE, EDUCATION § 7-305. ይህ በዚህ ገፅ በተዘረዘሩት ስነምግባሮች፡- ከክፍል መቅረት፣ መዘግየት፣ እና ዋልጌነት ተግባራዊ ይሆናል።

[2] የመቅረት ፈቃድ የሚያሰጡ ምክንያቶች፡- ቤተሰብ ውስጥ የሚያጋጥም ሞት፣ የተማሪዋ(ው) ወይም የተማሪዋ(ው) ልጅ ህመም፣ እርግዝና፣ እና ከወላጅነት ጋር የተያያዙ ሁኔታዎች፣ የፍርድ ቤት ጥሪ/ቀጠሮ፣ አደገኛ የአየር ሁኔታዎች፣ ሃይማኖታዊ በዓልን ለማክበር፣ የስቴቱ ድንገተኛ ሁኔታ፣ እገዳ፣ ትምህርት ቤቱ ስፖንሰር ያደረገው እንቅስቃሴ፣ እና በ MCPS ደንብ JEA-RA፣ ተማሪዎች በትምህርት ላይ ስለመገኘት ደንብ ላይ የተገለጹ ሌሎች ሁኔታዎች፥ COMAR። 13A.08.01.03.

[3]አንድ ተማሪ "ከትምህርት ቤት ሳያስፈቅድ የሚቀር" በማንኛውም ሩብ አመት ከ8 ቀኖች በላይ፣ በአንድ ሴሚስተር 15 ቀኖች፣ ወይም በትምህርት አመት ውስጥ 20 ቀኖች (በግምት 10%) ያለፈቃድ መቅረት ነው። MD. ANN.CODE, EDUCATION § 7-355.

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።<br>ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው) | | | | |
| ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል) | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | ደረጃ 2<br>በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | ደረጃ 3<br>በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
| **ብልግና/ድፍረት**<br>*ታዛዥ አለመሆን ከድፍረት ጋር ተጠቃልሏል። | ተገቢ ያልሆኑ ወይም ጎጂ የማፌዝ ምልክቶች ፣ የቃል ወይም የፅሁፍ አስተያየቶች፣ ወይም ምልክቶች ለሌሎች ማድረግ (ለምሳሌ፣ የቃል ስድብ፣ እርግማን፣ መልሶ መጨቃጨቅ)። | | | | |
| | በተደጋጋሚ ወይም ያለማቋረጥ የመምህራን፣ የሰራተኞች ወይም የአስተዳዳሪዎች መመሪያዎችን መቃወም ወይም አለመታዘዝ። | | | | |
| | | | | | |
| ረብሻ (704)<br>ስነምግባሩ የማያቋርጥና ልምድ ከሆነ እናም በመማርያ አካባቢ ታላቅ ተጽእኖ ካደረገ አጉል ድፍረት ወደ ረብሻ ሊሸጋገር ይችላል። | የመማር አካባቢን ሰላም በሚነሳ መለስተኛ መጥፎ ስነምግባር መጠመድ። | | | | |
| | ያለማቋረጥ ወይም አዘውትሮ ከትምህርት ትኩረት በሚነሳ ስነምግባር መሳተፍ/ማከናወን (ለምሳሌ፣ ያለተራ መናገር፣ ትናንሽ ነገሮች መወርወር፣ መራገጥ)። | | | | |
| | ከማስተማርና ከመማር የሚያዘናጋ እና የሌሎችን ደህንነት የሚነካ (ለምሳሌ፣ ጎጂ ነገሮችን መወርወር፤ አነሳሽ ቴክስቶች/የማህበራዊ ሚድያ መልእክቶችን መላክ ወይም መለጠፍ፤ ቪድዮዎች፤ የእሳት አደጋ ልምምድ/ስልጠና መረበሽ፤ በፈተና ወቅት ማቋረጥ፤ ሰራተኞችን መዝለፍ) ከመካከለኛ ወደ አሳሳቢ ስነምግባር መሳተፍ። | | | | |
| | ፀያፍ ቋንቋን መጠቀም ወይም በዘር፣ በሃይማኖት፣ በፆታ ማንነት ወይም በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት፣ የዘር ስድብን ጨምሮ፣ በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ መስተጓጎል ያስከትላሉ።[5] | | | | |

| ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል) | ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።<br>ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ደረጃ 1**<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | **ደረጃ 2**<br>በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | **ደረጃ 3**<br>በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | **ደረጃ 4**<br>በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | **ደረጃ 5**<br>የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
| **በግል ኤሌክትሮኒካዊ መሳርያዎች አላግባብ መጠቀም (802)**<br>**በአስቸኳይ ጊዜ ሁኔታ ወይም በቅድሚያ-ፈቃድ በተሰጠበት ሁኔታ ውስጥ አንድን መሳርያ መጠቀምን ማስወገድ።**[4]<br>*ይመልከቱMCPS ደንብ COG-RA፣ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያዎች/እቃዎች እና ፖሊሲ JHF፣ ጥቃት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት | የት/ቤትን ህግ ለመጻረር ወይም በት/ቤት መጥፎ ባህርይ ፎተግራፎችን/ቪድዮችን ለማሳየት የግል ሞባይል/ተንቀሳቃሽ መገልገያን በግትርነት መጠቀም። | | | | |
| | | የግል ሞባይልን መጠቀም ወይም ክፍት ማድረግ ተማሪው/ዋ ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው/ከተሰጣት በኋላ<br>ሳይበር ጉልበተኝነት ማለት በፖሊሲ JHF ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርቶች የሚያሟላ እና በተንቀሳቃሽ የመገናኛ መሳሪያ አማካኝነት ግለሰቦች ይዘትን እንዲያዩ ወይም እንዲያጋሩ በሚያስችል የኤሌክትሮኒክስ ግንኙነት የሚተላለፍ ጉልበተኝነት ማለት ነው።<br>(1) የሳይበር ጥቃት አንድ ሰው ላይ ሀፍረት ወይም ውርደትን የሚያስከትል የግል ገመና ወይም ግላዊ መረጃን ማሠራጨት፣ መለጠፍ ወይም ማዳረስን ያጠቃልላል።<br>(3) የሳይበር ጥቃት በትምህርት ቤት ቦታ ላይ ከተፈፀመ የዲሲፕሊን እርምጃ ጋር ሊያያዝ ይችላል፣ ትምህርት የሚሰጠው በአካል ወይም በኮምፒውተር (virtual) ቢሆንም በትምህርት ቤት የሚገኙ ተማሪዎች ላይ የጉዳት አደጋን ይፈጥራል፣ ወይም የትምህርት አሰጣጥ ሁኔታን ያውካል። | | | |
| | | | | | |
| **የአለባበስ ኮድ (706)**<br>የ MCPS ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶች እና ኃላፊነቶች፣ የሚጠበቅባቸውን የአለባበስ ስርዓት ይገልጻል። | ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው/ከተሰጣት በኋላ የአለባበስን ስነ-ስርአት የሚጥስ/የምትጥስ ተማሪ። | | | | |
| | ማስጠንቀቂያ ከተሰጠው/ከተሰጣት በኋላ የአለባበስን ስነ-ስርአት ደጋግሞ የሚጥስ/የምትጥስ ተማሪ። | | | | |

[4] የሌሎች የንግድ ማስታወቂያ የሌሎችን ግላዊነት የሚጥስ መረጃ ከሆነ፣የተማሪዎችን ጤና ወይም ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል፣ ብልግና ወይም ስድብ ከሆነ፣የትምህርት ቤት የሥራ እንቅስቃሴዎችን የሚያበላሽ ከሆነ፣ስራን የሚያስተጓጉል ከሆነ የግል ተንቀሳቃሽ መሳሪያ (PMD) በመጠቀም ሊተላለፍ አይችልም።

[5] PMD ማለት፡- መረጃን በድምጽ፣ በቪዲዮ ወይም በጽሑፍ ለመላክ ወይም ለመቀበል የሚያገለግል ከ MCPS ያልተሰጠ ማንኛውንም መሣሪያ ያመለክታል። ሞባይል ስልኮች፣ ኢ-ማንበቢያዎች (e-readers)፣ ታብሌቶች፣ የግል ኮምፒዩተሮች፣ ስማርት ሰዓቶች፣ ወይም ሌሎች ማይክሮፎኖች፣ የጆሮ ማዳመጫዎች፣ ድምጽ ማጉያዎች እና/ወይም ካሜራዎች ሁሉም PMD s ይባላሉ።

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)። ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው) | | | | |
| **ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል)** | **ደረጃ 1** በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | **ደረጃ 2** በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | **ደረጃ 3** በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | **ደረጃ 4** በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | **ደረጃ 5** የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
| **አልኮሆል (201)** **እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፣ ትምህርት ቤቱ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ ለማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም ለ MCPS የበሽታ መከላከያ እና ሕክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት።** *MCPS ደንብ IGO-RA፣ ስለ አልኮል መጠጥ፣ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ ተማሪዎችን የሚመለከቱ ሌሎች የአደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ መጠቀም ስለሚያስከትሏቸው ክስተቶች መመሪያ ይመልከቱ | | | **በአልኮል ተጽእኖ ስር መውደቅ።**[6፣8] | | |
| | | | **አልኮል መጠቀም ወይም ይዞ መገኘት**[6,8] | | |
| | | | **አልኮል ማሰራጨት/መሸጥ።**[7] | | |
| | | | | | |
| **የሚጨሱ እፆች(202)** **እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፥ ትምህርት ቤቱ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ ለማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም ለ MCPS የበሽታ መከላከያ እና ሕክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት።** *MCPS ደንብ IGO-RA፣የአልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ ተማሪዎችን የሚያካትቱ ሌሎች የአደንዛዥ ዕፅ አላግባብ መጠቀም መመሪያዎችን ይመልከቱ | | | **በሚጨሱ እፆች ተጽእኖ ስር መሆን።**[6፣8] | | |
| | | | **ሽታቸውን ማማግ/መሳብ/ማሽተት አጠቃቀም እና ይዞ መገኘት**[6,8] | | |
| | | | **የሚጤሱ እፆች ማሰራጨት/መሸጥ**[7] | | |

[6] ተማሪው(ዋ) በአልኮል፣ በአደገኛ ዕጾች፣ በደነዘዘ(ች) ሁኔታ ከተገኘ(ች) እና ትምህርት ቤት ውስጥ የጤና አገልግሎት የሚሰጥ ከሌለ፥ ተማሪን ወደ ቤት መላክ እና ወደ ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ ወይም ወደ ማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ ማስተላለፍ አስፈላጊ ይሆናል። ተማሪው(ዋ)ን ወደ ቤት ከመላክ በፊት፣ ተማሪው(ዋ) የት/ቤቱን ግቢ ሲለቅ/ስትለቅ በአንድ የቤተሰብ አባል ወይም ለመርዳት በሚችል ግለሰብ መታጀቡን/መታጀቧን ለማረጋገጥ ት/ቤቱ ጥንቃቄ መውሰድ ያስፈልጋል። የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ደንብ MCPS Policy IGN አልኮል፣ ትምባሆ፣ እና ሌሎች ጎጂ መድሃኒቶች ህገ-ወጥ አጠቃቀም በሞንጎሞሪ ካውንቲ ት/ቤቶች መከልከል Preventing Alcohol, Tobacco, and Other Drug Abuse in Montgomery County Public Schools በተጨማሪ ይመልከቱ።

[7] የት/ቤት የስነስርአት ማስከበር ጉዳይን በሚመለከት፣ አልኮል፣ የሚጤሱ፣ ወይም መድሀኒቶች/የተከለከሉ እፆችችን ስርጭት፣ ሽያጭ ወይም የመሸጥ አዝማምያ።

[8] ለመረጃ ያክል፣ የአካል ጉዳተኝነት ላላቸው ተማሪዎች ብቻ፡በኮድ 892 ተጠቀሙ። (ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች የ"ህገወጥ እፆች" ትርጉም በህጋዊ መንገድ ያልተ ገኙ ነገሮች፣ ህጋዊ ፈቃድ ባለው የጤና ባለሙያ ቁጥጥር ብቻ አገልግሎት ላይ የሚውል፣ ወይም ቁጥጥር የሚያስፈልጋቸው መዳኒቶች አዋጅ ወይም በሌላ ፌደራል ህግ እውቅና በሰጠው ባለስልጣን ቁጥጥር አገልግሎት ላይ የሚውል ማለት ነው።)

**ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።**

ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው)

| ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል) | ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | ደረጃ 2<br>በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | ደረጃ 3<br>በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | ደረጃ 4<br>በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5<br>የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
|---|---|---|---|---|---|
| **መድሀኒቶች/የተከለከሉ ነገሮች (203)**<br>**እንደ ማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፥ ትምህርት ቤቱ ለሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምሪያ፣ ለማህበረሰብ አገልግሎት ሰጪ፣ ወይም ለ MCPS የበሽታ መከላከያ እና ሕክምና ፕሮግራም ማስተላለፍ አለበት።**<br>*MCPS ደንብ IGO-RA፣አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ ተማሪዎችን የሚመለከቱ ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ የመጠቀም ክስተቶችን እና ደንብ JPC-RA፣ለተማሪዎች የመድሃኒቶች አሰጣጥየሚመለከቱ መመሪያዎችን ይመልከቱ | | **ያልተፈቀደ አጠቃቀም፣ ይዞ መገኘት፣ ወይም በሕገ-ወጥ ዕፆች ተጽዕኖ ሥር መሆን** [6,8,9] **(ለምሳሌ፡- በሐኪም የሚታዘዝ ወይም በሐኪም ያልታዘዘ የህክምና መድኃኒት)።** | | | |
| | | | **ሕገወጥ ዕጾች ተጽዕኖ ሥር መውደቅ፣ ይዞ መገኘት፣ ወይም መጠቀም።** [6,8,9] | | |
| | | | **ህጋዊ ያልሆኑ ወይም ህገ-ወጥ መድኃኒቶችን ማሠራጨት ወይም መሸጥ** (Juuls፣ Vapes፣ e-cigarettes፣ Edibles **ያካትታል)።** [6,7] | | |
| | | | | | |
| **ትምባሆ (204)**<br>**እንደማንኛውም የስነስርአት ርምጃ፣ ለመከላከልና ለማረም/ለማከም፣ ት/ቤቱ ለሞንጎሞሪ ካውንቲ** (MCPS) **የጤና እና የሰብአዊ አገልግሎቶች መምርያ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ ወይም ወደ አንድ የ**MCPS **ፕሮግራም ማስተላለፍ ይኖርበታል።**<br>*MCPS ደንብ IGO-RA፣ የአልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ፣ተማሪዎችን የሚያካትቱ ሌሎች የአደንዛዥ እጾች አጠቃቀም ክስተቶች እና የMCPS ደንብ COF-RA MCPS ንብረት ላይ አልኮሆል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች መድሃኒቶችን ስለመጠቀም መመሪያዎችን ይመልከቱ | **ትንባሆ በማንኛውም መልኩ መጠቀም ወይም መያዝ** (JUUL **መሳሪያዎችን፣ ቫፕስ፣ ኢ-ሲጋራዎች እና የሚታኙትን ጭምር)።** | | | | |
| | | | | | |
| **በትምህርት ማጭበርበር/ አለመታመን (801)**<br>* ስለ ውጤት አሰጣጥ እና ሪፖርት አሰጣጥ የ MCPS ደንብ IKA-RA የሚያስከትለውን የውጤት አሰጣጥ መዘዞች ይመልከቱ። | **የሌላ ሰውን ስራ ወይም ሀሳብ መውሰድን የመሰለ የራስ እስመስሎ ማቅረብ (3ኛ-12ኛ ክፍል ተማሪዎች)፤ የመምህር ወይም የወላጅ/አሳዳጊ ፊርማ የመሰለ የሀሰት ተግባር፣ ወይም ማታለል።**<br>**በግምገማዎች ወይም በሌሎች ማርክ የተሰጠባቸው ስራዎች ላይ የተያዙ መረጃዎች መጋራት ወይም ማሰራጨት።** | | | | |
| | | **የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (**MCPS**) የኮምፒውተር አውታር ወይም ፈተናዎችን ያለፈቃድ መጎርጎር/መፈተሽ ወይም ሌላዉ/ዋን ያለፈቃድ መጎርጎር/መፈተሽን ማገዝ።**<br>**በተደጋጋሚ ወይም በስፋት ግምገማ/ፈተና የሚሰጥባቸውን መረጃዎች/ ኢንፎርሜሽን ማሠራጨት።** | | | |

[9]ለመረጃ አያያዝ እንዲመች፣ የአካል ጉዳት ላላቸው ልጆች ብቻ፣ በ21 U.S.C. § 812; 21 C.F.R. pt. 1308 ቁጥጥር የሚደረግባቸው መዳኒቶች ዝርዝሮች ውስጥ የተለዩ እፆች ወይም ነገሮች ስለመሸጥ በኮድ ቁጥር 891 ይጠቀሙ።

<table>
<tr><th></th><th colspan="5">ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።<br><br>ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው)</th></tr>
<tr><th>ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል)</th><th>ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር)</th><th>ደረጃ 2<br>በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ )</th><th>ደረጃ 3<br>በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች)</th><th>ደረጃ 4<br>በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ)</th><th>ደረጃ 5<br>የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር)</th></tr>
<tr><td rowspan="3">ስርቆሽ (803)<br>ት/ቤቶች የሚከተሉትን ታሳቢዎች ማገናዘብ አለባቸው።<br>• የተማሪ እድሜ<br>• ንብረቱን ለመውሰድ የተማሪው/ዋ አላማ<br>• የንብረቱ ዋጋ በገንዘብ ቢተመን፣<br>• ተማሪው/ዋ ሆን ብሎ/ላ አስቀድሞ የጠነሰሰ/ችው ሳይሆን፣ በወቅቱ አጋጣሚ ሁኔታ ፈፅሞት/ማው እንደሆነ<br>• ተማሪው/ዋ ንብረቱ ዋጋ ያለውና ለመተካት ውድ መሆኑን ያ/ታውቅ እንደሆነ<br>• ንብረቱ ተመልሶ ወይም ተገኝቶ እንደሆነ</td><td colspan="2">ባለቤቱ ሳይፈቅድ እና/ወይም ሳያውቀው የሌላን ንብረት መውሰድ ወይም ማግኘት።</td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td colspan="2">ያለማቋረጥ ወይም በዘልምድ የሌላን ሰው ንብረት ያለ ባለቤቱ ፈቃድ እና/ወይም ባሌቤቱ ሳያውቅ መውሰድ ወይም ማግኘት።</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td colspan="2">ስርቆቱን በተለይ ከባድ የሚያደርገው በተዘረዘሩት ታሳቢዎች ሆኖ፣ የሌላን ሰው ንብረት ያለ ባለቤቱ ፈቃድ እና/ወይም ባለቤቱ ሳያውቅ መውሰድ ወይም ማግኘት።</td><td></td></tr>
<tr><td colspan="6"></td></tr>
<tr><td rowspan="3">የንብረት መውደም (806)<br>ት/ቤቶች የሚከተሉትን ታሳቢዎች ማገናዘብ አለባቸው፡-<br>• የወደመው ንብረት የገንዘብ ዋጋ<br>• ተማሪው/ዋ ንብረቱ ዋጋ ያለውና ለመተካት ውድ መሆኑን ያ/ታውቅ እንደሆነ<br>• የተማሪው እድሜ<br>• ተማሪው/ዋ ሆን ብሎ/ላ አስቀድሞ የጠነሰሰ/ችው ሳይሆን፣ በወቅቱ አጋጣሚ ሁኔታ ፈፅሞት/ማዉ እንደሆነ<br>• ተማሪው/ዋ ንብረቱን ያወደመ/ችበት ምክንያት</td><td>ድንገተኛ ጉዳት ማድረስ።</td><td></td><td></td><td></td><td></td></tr>
<tr><td></td><td colspan="4">የሚወሰደው የሥነ-ሥርዓት ርምጃ የሚወሰነው በተዘረዘሩት ታሳቢዎች መሰረት ሆኖ፣ በሞንጎመሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶች (MCPS)፣ ሰራተኞች፣ ወይም ሌሎች ተማሪዎች ንብረት ላይ ሆን ብሎ ጉዳት ማድረስ።</td></tr>
<tr><td></td><td colspan="4">ፀያፍ ቋንቋን መጠቀም ወይም በዘር፣ በሀይማኖት፣ በፆታ ማንነት ወይም በፆታዊ ዝንባሌ ላይ የተመሰረተ ጥላቻን ወይም መድልዎን የሚያበረታቱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት፣ የዘር ስድብን ጨምሮ፣ በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ስራዎች ወይም እንቅስቃሴዎች ላይ ከፍተኛ ረብሻ ይፈጥራል ተብሎ የሚገመት ድርጊት።</td></tr>
<tr><td colspan="6"></td></tr>
<tr><td>ወሲባዊ ተግባር (603)<br>እንደማንኛውም የስነስርአት ርምጃ፣ የት/ቤቱ ሰራተኞች ተማሪዎችን ወደሚመለከተው የምክር አገልግሎት መምራት አለባቸው።</td><td></td><td colspan="3">ተገቢ ያልሆነ ወሲብ ቀስቃሽ ባህርይ (ለምሳሌ፡-ሰውነት መጋለጥ፣ ወሲባዊ ቴክስቶችን መጻጻፍ፣ ወሲባዊ ድርጊቶችን በት/ቤት ንብረት ውስጥ ማድረግ)።</td><td></td></tr>
</table>

| ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል) | ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)። ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | **ደረጃ 1** በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | **ደረጃ 2** በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | **ደረጃ 3** በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | **ደረጃ 4** በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | **ደረጃ 5** የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
| **ወሲባዊ ጥቃት (601)** እንደማንኛውም የስነስርአት ርምጃ፣ የት/ቤቱ ሰራተኞች ተማሪዎችን ወደሚመለከተው የምክር አገልግሎት መምራት አለባቸው። | | | በአካላዊ፣ በጾታዊ በሚያስገደድ ዓይነት በሌላዉ ስነምግባር ውስጥ መሳተፍ። በአካላዊ በጾታዊ ጥቃቅን በሆኑ ሌሎች አካላዊ ባህሪያት ውስጥ መሳተፍ። | | |
| | | | | | |
| **ፆታዊ ወከባና ጥቃት (602)** የወሲባዊ ጥቃት ወይም የወሲባዊ ትንኮሳ ተጠርጣሪ ክስ እንደማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል፥ ትምህርት ቤቶች የተማሪ ደህንነት እና ሥነ-ሥርአት የማስከበር ክፍል Title IX አስተባባሪን ማነጋገር አለባቸው፤ የቦርድ ፖሊሲ "Board Policy ACF" ድንጋጌ መሠረት የትምህርት ቤት የድጋፍ እርምጃዎች አወሳሰድና ምርመራ ከፌዴራል እና ከስቴት ሕግ ጋር የሚጣጣም መሆኑን ማረጋገጥ ተገቢ ይሆናል፥ የተማሪዎች ወሲባዊ በደል እና ወሲባዊ ትንኮሳ፣ የቦርድ ፖሊሲ ACI - "Board Policy ACI" የሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ ፥ የቦርድ ፖሊሲ JHF - "Board Policy JHF" ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት፥ የ MCPS ደንብ JHF-RA፥ በተማሪ ላይ ጉልበተኛነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት፥ እና MCPS ቅፅ 230-35፣ ስለ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ። | | ተቀባይነት የሌለው ወሲባዊ እርምጃ፣ የወሲብ ውለታ ጥያቄዎች፣ እና/ወይም ሌላ ተገቢ ያልሆነ የቃል፣ የጽሑፍ፣ ወይም ወሲባዊ ባህሪ ያለው አካላዊ መገዳደር፣ የጾታ ብልግና ወይም ወሲባዊ ትንኮሳ ሊሆን ይችላል። (ከ Title IX አስተባባሪ ጋር በመመካከር ትምህርት ቤቶች ተገቢውን ህጋዊ አካሄድ እና የሚያስከትሉትን መዘዞች ለመወሰን ዕድሜን፣ የክፍል ደረጃን፣ የእድገት ደረጃን፣ ቀደም ያሉ ጥፋቶችን፣ ሆን ተብሎ የተደረገ እና ሌሎች ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት ተገቢ እርምጃ ይወስዳሉ) | | | |

<table>
<tr><td></td><td colspan="5">ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።<br>ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው)</td></tr>
<tr><td>ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል)</td><td>ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር)</td><td>ደረጃ 2<br>በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ )</td><td>ደረጃ 3<br>በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች)</td><td>ደረጃ 4<br>በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ)</td><td>ደረጃ 5<br>የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር)</td></tr>
<tr><td rowspan="4">ማሸማቀቅ/ወከባ<br>የማንኛውም የዲሲፕሊን እርምጃ አካል በማድረግ፣ ት/ቤቶች በማስተካከያ ስልቶች ላይ ማተኮር እና ተማሪዎችን ተገቢ ካውንስሊንግ ወደሚያገኙበት መምራት አለባቸው።<br>*የቦርድ ፖሊሲ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ እና MCPS ደንብ JHF-RA፣ የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት፣ ይመልከቱ። እና MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪያ ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ</td><td rowspan="3"></td><td colspan="4">ጉልበተኝነት ማለት በተማሪዎች መካከል ያልተፈለገ፣ ወራዳ ባህሪ ማለት በፖሊሲ JHF የተከለከለ ስነምግባር መስፈርት የሚያሟሉ እና የሚከተሉትን ያጠቃልላል—<br>(1) የሀይል አለመመጣጠን (ጉልበተኞች አካላዊ፣ ስሜታዊ፣ ማህበራዊ ወይም አካደሚያዊ ሀይላቸውን ተጠቅመው ሌሎችን ለመቆጣጠር፣ ለማግለል ወይም ለመጉዳት ሲያውሉት)፤ እና<br>(2) ድግግሞሽ (ከአንድ ጊዜ በላይ የተከሰቱ የጉልበተኝነት ባህሪያት ወይም በሚሰበሰቡ መረጃዎች ሊረጋገጡ የሚችሉ የመደጋገም ዕድላቸው ከፍተኛ የሆነ ጉልበተኝነትን ማሳየት)።<br>ለሳይበር ጥቃት፣ “ተገቢ ያልሆነ የግል ኤሌክትሮኒክስ አጠቃቀምብ” በገፅ 14 ላይ በተጨማሪ ይመልከቱ።</td></tr>
<tr><td colspan="4">ትንኮሳ ማለት በቦርድ ፖሊሲ ACA ላይ እንደተገለጸው በፖሊሲ JHF ውስጥ የተከለከሉ ድርጊቶችን መስፈርት የሚያሟሉ እና የአንድን ግለሰብ ትክክለኛ ወይም የመሰላቸውን የግል ባህሪያትን ተሞርኩዞ ሌላ ግለሰብን ማስቀየም፣ መሳለቂያ ማድረግ ወይም ማዋረድ ማለት ያለአግባብ የሚፈፀሙ አሉታዊ ድርጊቶች ማለት ነው፣ ከአድሎአዊነት የነፃ፣ ፍትሃዊነት፣ እና የባህል ብቃት ፣ ወይም በተፈጥሮ ወሲባዊ የሆኑ፣ በቦርድ ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ጾታዊ በደል እና ጾታዊ ትንኮሳ ፣ ወይም የቦርድ ፖሊሲ ACI፣ የሰራተኞች ጾታዊ ትንኮሳ ፣ የተማሪው(ዋ) የሰውነት ክፍሎች የተጋለጠበት ወይም በግብረ-ሥጋ ግንኙነት ተግባር ላይ እያለ(ች) የሚያሳይ የተማሪን ምስሎችን ያካትታል።</td></tr>
<tr><td colspan="4">ማስፈራራት ማለት በፖሊሲ JHF የተከለከለ የስነምግባር መስፈርቶችን የሚያሟሉ እና የፍርሃት እና/ወይም የበታችነት ስሜትን የሚያስፈራራ ወይም የሚያነሳሳ በሌላ ግለሰብ ላይ የሚደረግ ማንኛውም ግንኙነት ወይም እርምጃ ነው። የበቀል እርምጃ እንደ ማስፈራራት ሊቆጠር ይችላል።</td></tr>
<tr><td colspan="5">ፀያፍ ቋንቋ መጠቀም ወይም ጥላቻን የሚያራምዱ ምስሎችን እና/ወይም ምልክቶችን ማሳየት እንደ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ ወይም ማስፈራራት ሊቆጠር ይችላል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው።</td></tr>
<tr><td colspan="6"></td></tr>
<tr><td>በኃልማሳ ላይ የሚደረግ ዛቻ (403)<br>በተማሪ ላይ የሚደረግ ዛቻ (404)<br>ትምህርት ቤቶች የአስጊ ስነምግባር/ባህርይ ምርመራ ማካሄድ አለባቸው።<br>*ይመልከቱ፡- MCPS Regulation COA-RA፣Behavior Threat Assessment.[10]</td><td colspan="4">የዛቻ ቋንቋ (የቃል ወይም የፅሁፍ/ኤሌክትሮኒክ፤ በውስጠታዋቂ ወይም በግልፅ) ወይም በ ሰራተኛ አባል፣ ተማሪ፣ ወይም ሌላ ላይ ያተኮረ አካላዊ እንቅስቃሴ።</td><td></td></tr>
</table>

[10] የባህሪ ስጋት ምርመራዎች የት/ቤቱን የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ አስፈላጊነት መገደብ የለባቸውም።

**ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።**

ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ:- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው)

| ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል) | ደረጃ 1 በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | ደረጃ 2 በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዜያዊ እገዳ ) | ደረጃ 3 በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | ደረጃ 4 በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | ደረጃ 5 የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
|---|---|---|---|---|---|
| **ማስገደድ/ማስፈራራት (406)** ትምህርት ቤቶች የአስጊ ስነምግባር/ባህርይ ምርመራ ማካሄድ አለባቸው። *ይመልከቱ:- MCPS Regulation COA-RA፣ Behavior Threat Assessment.[10] | | አንድ ሰው ንብረቱን እንዲያስረክብ በዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ወይም በሃይል (ያለመሳርያ) መጠቀም። | | | |
| | | አንድ ሰው ንብረቱን እንዲያስረክብ በዛቻ፣ ማስፈራራት፣ ወይም በሃይል (በመሳርያ) መጠቀም። | | | |
| **የውሸት አደጋ ጥሪ (502)** | | ያለምንም ምክንያት የእሳት ወይም ሌላ አይነት አደጋ ማስጠንቀቂያ መቀስቀስ፣ በቴሌፎንም ሆነ በግለሰብ ደረጃ (ለምሳሌ፣ የእሳት አደጋ ማስጠንቀቂያ መጥርያ በመለኮስ፣ በ911 ያለአግባብ መደወል)፤ የእሳት ማጥፍያ መሳርያ ያለምንም ምክንያት መርጨት/ማርከፍከፍ። | | | |
| **የቦምብ ዛቻ (502)** ትምህርት ቤቶች የአስጊ ስነምግባር/ባህርይ ምርመራ ማካሄድ አለባቸው። *ይመልከቱ:- MCPS Regulation COA-RA፣Behavior Threat Assessment.[10] | | የቦምብ ዛቻ ማድረግ ወይም በት/ቤት ተኩስ የመክፈት ማስፈራራት። | | | |
| **ህግ/ደንብ/ድንበር መጣስ/መተላለፍ (804)** *MCPS ንብረት ላይ MCPS ደንብ COC-RA፣ መተላለፍን ወይም ሆን ብሎ ማወክን ይመልከቱ | | ከትምህርት ቤት መታገድ ወይም መባረርን ጨምሮ በማንኛውም MCPS ንብረት ላይ ያለ ፍቃድ መገኘት። | | | |
| | | | | ብጥብጥ ለመፍጠር፣ ለመደባደብ፣ ሌላ ተማሪን ወይም ሰራተኛን ለማጥቃት ወይም ንብረት ላይ ጉዳት ለማድረስ በማሰብ መተላለፍ። | |
| **በጎልማሳ ላይ ጥቃት/አደጋ (401)** | | የ MCPS ሠራተኛ ወይም ሌላ ጎልማሳ በረብሻ ወይም በሌላ ሁከት ምክንያት ለመገላገል የገባ(ች) ሠራተኛን ሆን ብሎ መምታትን ጨምሮ አካላዊ ጥቃት ማድረስ (መደብደብ)። | | | |

[10] የባህሪ ስጋት ምርመራዎች የት/ቤቱን የዲሲፕሊን እርምጃ መውሰድ አስፈላጊነት መተካት/መገደብ የለባቸውም።

<table>
<tr><td></td><td colspan="5">ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)።<br>ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው)</td></tr>
<tr><td>ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል)</td><td>ደረጃ 1<br>በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር)</td><td>ደረጃ 2<br>በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ )</td><td>ደረጃ 3<br>በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች)</td><td>ደረጃ 4<br>በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ)</td><td>ደረጃ 5<br>የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር)</td></tr>
<tr><td rowspan="3">ድብድብ/ግጭት (405)<br>ተማሪ ላይ አደጋ/ጥቃት (402)<br>ት/ቤቶች የሚከተሉትን ጨምረው በርካታ ታሳቢዎችን ማገናዘብ አለባቸው፡-<br>• ተማሪው/ዋ አስቀድሞ/ማ ያሰበ(ች)ው/ያቀደችው ሳይሆን በወቅቱ ባጋጠመ ሁኔታ ተነሳስቶ/ታ ፈፅሞት ፈጽማዉ እንደሆነ<br>• ተማሪው(ዋ)ን በቃል ማናደድ ወይም ተማሪው(ዋ) ሌሎች እንዲጣሉ/እንዲደባደቡ ማነሣሣት<br>• ተማሪው/ዋ ራስን ለመካላከል አድርጎት/ጋዉ አንደሆነ<br>• ተማሪው/ዋ በድብድብ ጠብ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ/ታ ነበር ወይ<br>*የቦርድ ፖሊሲ ይመልከቱ JHF፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ እና MCPS ደንብ JHF-RA፣ የተማሪ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራራት፣ እና MCPS ቅጽ 230-35፣ ጉልበተኝነት፣ ትንኮሳ፣ ወይም ማስፈራሪትን ሪፖርት ማቅረቢያ ቅጽ<br>** የ MCPS ደንብ JHG-RA፣ ወንበዴዎች፣ የወሮበሎች እንቅስቃሴ፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ አጥፊ ወይም ህገወጥ ቡድን ባህሪ መከላከል፣ የ MCPS ቅጽ 230-37፣ ከወሮበላ ቡድን ጋር የተዛመደ ክስተት ሪፖርት ማድረግያ ቅጽ</td><td colspan="3">ሌላ ሰው ላይ መገፍተር፣ መግፋት ወይም አካላዊ ጉዳት መፈፀም (ለምሳሌ፣ የሰውነት ፍተሻ፣ ሆን ብሎ መጋጨት፣ ነገር ግን እርግጫን አይጨምረም)።</td><td></td><td></td></tr>
<tr><td colspan="4">ድንገተኛ እና/ወይም አጭር፣ እና በመለስተኛ ቁረጣ፣ ጭረት፣ እና ሰንበር በሚያስከትል ጠብ ወይም ድብድብ መሳተፍ።</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td colspan="3">ሆን ተብሎ ድብድብ ላይ መሳተፍ፣ ይህም ትልቅ፣ አስቀድሞ የታቀደ፣ የተራዘመ እና/ወይም እጅና እግር የመሰበር ከባድ ጉዳቶችን ሊያስከትል ወይም በተዘረዘሩት ምክንያቶች ከባድ ሊሆን ይችላል።</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ከባድ የአካል ጉዳት (408)<br>ከፍተኛ የሆነ ለሞት የሚያደርስ አደጋ፣ ከፍተኛ የአካል ህመም፣ ረዘም ያለ ወይም ግልጽ የአካል ጉዳትን የሚያስከትል ማንኛውም ጉዳት፣ ወይም ማንኛውም የአካል ማጉደል፣ የአካል ክፍል ወይም የአእምሮ አካል ክፍልን ማጣት።</td><td></td><td colspan="3">ሳይታሰብ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም ንቃተ ህሊና መሣትን በሚያስከትል ድርጊት ላይ መሳተፍ።</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td></td><td></td><td colspan="2">ሆን ብሎ ከባድ የአካል ጉዳት ወይም የህሊና መሣት በሚያስከትል ድርጊት ላይ መሳተፍ።</td></tr>
<tr><td rowspan="2">ንብረት ማጥፋት/ማቃጠል (501)</td><td colspan="4">በሌሎች ላይ አደጋ ለማድረስ ታስቦ ሳይሆን እሳት መለኮስ ወይም ለመለኮስ መሞከር ወይም ሌሎች ሲሎኩሱ ማገዝ።</td><td></td></tr>
<tr><td></td><td colspan="4">ሆን ብሎ ሌሎች ላይ አደጋ ለመጣል ወይም ንብረት ለማውደም እሳት መለኮስ ወይም ለመለኮስ መሞከር ወይም ሌሎች ሲሎኩሱ ማገዝ።</td></tr>
</table>

| | ስለ እያንዳንዱ ባህሪ የሚፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎች ተዘርዝረዋል፣ እና መጀመሪያ ከዝቅተኛው ደረጃ መነሳት ግምት ውስጥ መግባት አለበት (ገጽ 11 ይመልከቱ)። ከባህሪ ዝርዝር ቀጥሎ ያሉት ጥቁር ምልክቶች ያልተፈቀዱ የባህሪ ማስተካከያዎችን ያመለክታሉ (ለምሳሌ፡- ባህሪው ደረጃ 3 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት በትምህርት ቤት ውስጥ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ሲሆን፣ በተመሳሳይ መልኩ በደረጃ 4 ስር ያለ ጥቁር ምልክት ማለት ለአጭር ጊዜ ማገድ/ማስወጣት አይፈቀድም ማለት ነው) | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| **ተገቢ ያልሆነ ወይም ረባሽ ባህሪ (በስቴቱ የእገዳ ኮድ ተደንግጓል)** | **ደረጃ 1** በመማርያ ክፍልና በመምህር የሚመሩ ርምጃዎች (ለምሳሌ፡ በፅሁፍ ይቅርታ መጠየቅ፣ ከት/ቤት የምክር አገልግሎት ሰጭ ጋር መወያየት፣ መታሰር) | **ደረጃ 2** በመምህሩ(ሯ)-የሚመራ/ወደ ቀጣይ ደረጃ ማስተላለፍ እና በአስተዳደር የተደገፉ እርምጃዎች (ለምሳሌ፣ የማህበረሰብ አገልግሎት፣ የጓደኞች ገላጋይነት፣ ከመማርያ ክፍል ጊዝያዊ እገዳ ) | **ደረጃ 3** በአስተዳደር የተደገፈ እና ወይም የማስወገድ እርምጃዎች (ለምሳሌ፡ የተሐድሶ ተግባሮች፣ በት/ቤት ውስጥ እገዳ፣ በት/ቤት ውስጥ የባህሪ ማስተካከያ እርምጃዎች) | **ደረጃ 4** በአስተዳደራዊ ውሳኔ የተደገፉ ለአጭር ጊዜ ከትምህርት ቤት ውጪ የማግለል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የተሐድሶ ተሞክሮዎች፣ የምክር ፕሮግራሞች፣ የአጭር ጊዜ እገዳ) | **ደረጃ 5** የረጅም ጊዜ በአስተዳደራዊ ድጋፍ ከትምህርት ቤት ውጪ ማግለል እና ሪፈራል ምላሾች (ለምሳሌ፥ የረጅም ጊዜ እገዳ፣ ማባረር) |
| **የጦር መሳሪያዎች (301)** | | | | | ሽጉጥ መያዝ (ለምሳሌ፡- የእጅ ሽጉጥ)[11] |
| **ሌሎች ጠመንጃዎች (302)** | የጦር መሳሪያ ተመሳሳይ ስሪት፣ ሽጉጥ መሰል አሻንጉሊቶችን እና/ወይም ሌሎች ተመሳሳይ ነገሮችን፣ ውሃ የሚረጭ ሽጉጥ መያዝ፣ መጠቀም እና/ወይም ማስፈራራት።[11] | | | | |
| | | እውነተኛ ያልሆነ ሽጉጥ (ቢቢ፣ ፔሌት፣ ካፕ፣ ወይም ኤርሶፍት ሽጉጥ የመሳሰሉ) ወይም ሽጉጥ የመሰለ አሻንጉሊት መያዝ፣ መጠቀም ወይም ለመጠቀም ማስፈራራት።[11] | | | |
| **ቢላዎችና ሌሎች ጦር መሳርያዎች (303)** *ይመልከቱየMCPS ደንብ COE-RA፣ የጦር መሳርያዎች/Weapons/ | በመሳርያ የመጠቀም አላማ ሳይኖር፣ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ቢላዋ ወይም ሌላ መሳርያ መያዝ። | | | | |
| | | ሆነ ብሎ እንደመሳርያ ለመጠቀም፣ በሰው አካል ላይ ከባድ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ቢላዋ ወይም ሌላ መሳርያ መያዝ። | | | |
| | | | ቢላዋ ወይም ሌላ መሳርያ ይዞ በአካል ላይ ጉዳት ለማድረስ ማስፈራራት። | | |
| **ፈንጂዎች (503)** | በሰው እና በንብረት ላይ ጉዳት ማድረስ የሚችሉ፣ ከጠመንጃ ሌላ፣ የሚፈነዳ መሳርያ፣ ነገር ወይም የሆነ የሚቃጠልና የሚፈነዳ ነገሮች መያዝ (ለምሳሌ፡- ርችት፣ የጢስ ቦምብ፣ ብልጭታ ነገሮችን፤ እንደ ረብሻ የሚቆጠሩትን ነገር ግን "snap pops" አያካትትም)። | | | | |
| | | | | እላይ እንደተገለጸው፣ ፈንጂ ወይም የሚፈነዳ ነገር መሳርያ ወይም ማፈንዳት ወይም መያዝና ለማፈንዳት ማስፈራራት። | |

[11]በፌደራል እና በሜሪላንድ ስቴት ህግ መሰረት፡-
የጦር መሳርያ ይዞ/ዛ ወደ ት/ቤት የመጣ/ች ተማሪ "ቢያንስ ለ1 አመት ከት/ቤት ይወገዳል/ትወገዳለች፣ ነገር ግን አንድ የካውንቲ የበላይ ተቆጣጣሪ "የካውንቲው ቦርድ የትምህርት አማራጮችን ካፀደቀ፣ እያንዳንዱን ጉዳይ በየቅል እየለየ፣ አጠር ያለ የማሰናበቻ ጊዜ ወይም የትምህርት አማራጭ ሊወሰን ይችላል።" MD. ANN. CODE, EDUCATION § 7-305(f)(2)-(3); COMAR 13A.08.01.12-1. የሆነ ሆኖ፣ የጦር መሳርያ ይዞ ወደ ት/ቤት የመጣ የአካል ጉዳት ያለው ተማሪ ዲሲፕሊን፣ እገዳ፣ ስንብት፣ ወይም ጊዜያዊ አማራጭ ምደባ የሚፈፀመው የIDEA ግደታዎችን በመከተል ነው። MD. ANN. CODE, EDUCATION § 7-305(g); COMAR 13A.08.01.12-1(C). ለመረጃ አይያዝ አንዲመች፣ የአካል ጉዳተኝነት ላላቸው ተማሪዎች ኮድ 893 ይመለከቷል።

# የተማሪ ባህሪይ ማስተካከያ፣ ሠላም እና ደህንነትን በሚመለከት የትምህርት ቦርድ ፖሊሲዎች እና የ MCPS ደንቦች

Policy ACA፣ ከአድሎአዊነት የነፃ፣ ፍትሃዊነት፣ እና የዳበረ ባህል
ፖሊሲ ACF፣ የተማሪዎች ወሲባዊ ጥቃት እና ወሲባዊ ትንኮሳ
ፖሊሲ ACI፣ የሰራተኞች ወሲባዊ ትንኮሳ
ፖሊሲ COA፣ የተማሪ ደህንነት እና የትምህርት ቤት ሠላም
ፖሊሲ EEA፣ ስለተማሪ መጓጓዣ
ፖሊሲ IGN፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ውስጥ አልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ መጠቀምን መከላከል
መመርያ JFA፣ የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች
ፖሊሲ JGA፣ የባህሪ ማስተካከያዎች፣ ደህንነት እና ጤናማነት ዕቅድ
መመርያ JHF፣ ጥቃት፣ ትንኮሳ/ወከባ፣ ወይም ማስፈራራት
ደንብ ACA-RA፣ ከአድሎአዊነት የነፃ፣ ፍትኃዊነት እና የባህል ብቃት
ደንብ ACF-RA፣ ታይትል IX የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ተማሪዎች ጾታዊ ትንኮሳ ምርመራ
ደንብ ACG-RB፣ "Section 504 of the Rehabilitation Act of 1973" መሠረት ለሚገባቸው ተማሪዎች ተገቢ መገልገያ ዎችና ማሻሻያዎች
ደንብ COA-RA፣ የሚያስፈራ/የሚያሰጋ ባህርይን መመርመር
ደንብ COC-RA፣ የሞንጎሞሪ ካውንቲ የሕዝብ ት/ቤቶችን (MCPS Property) ንብረት መድፈር/የንብረት ድንበር መተላለፍ እና ሆን ተብሎ ረብሻ
ደንብ COE-RA፣ የጦር መሳርያዎች
ደንብ COF-RA፣ አልኮሆል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች መድሃኒቶችን በሞንትጎመሪ ካውንቲ የህዝብ ትምህርት ቤቶች ንብረት ላይመጠቀም
ደንብ COG-RA፣ የግል ተንቀሳቃሽ መገልገያዎች
ደንብ ECC-RA፣ በሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ ንብረት  መጥፋት ወይም መበላሸት
ደንብ EEA-RA፣ የተማሪ መጓጓዣ
ደንብ EEB-RA፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ አውቶቡሶችን በጥንቃቄ ማሽከርከር
ደንብ IGO-RA፣ የአልኮል፣ ካናቢስ፣ ትምባሆ እና ሌሎች ተማሪዎችን የሚያካትቱ አደንዛዥ ዕፆችን አላግባብ የመጠቀም ክስተቶች መመሪያ
ደንብ IGT-RA፣ የኮምፒውተር አጠቃቀም፣ ኤሌክትሮኒክ መረጃዎች፣ እና የመገናኛ አውታር ደህንነት የተጠቃሚ ሀላፊነቶች
ደንብ IOI-RA፣ ለተለዋጭ/አማራጭ ፕሮግራሞች የምደባ ሂደት
ደንብ JEA-RA፣ የትምህርት ክትትል
ደንብ JEE-RA፣ የተማሪ ዝውውሮች እና አስተዳደራዊ ምደባዎች
ደንብ JFA-RA፣ የተማሪ መብቶችና ሀላፊነቶች
ደንብ JGA-RA፣ የተማሪ ባህሪ ማስተካከያዎች
ደንብ JGA-RB: እገዳና ስንብት
ደንብ JGA-RC፣ የአካል ጉዳተኝነት ያላቸውን ተማሪዎች እገዳና ስንብት
ደንብ JGB-RA፣ ፍተሻ እና መያዝ/መውረስ
ደንብ JHF-RA፣ ተማሪን ማስጨነቅ፣ ማስፈራራት፣ ወይም ወከባ
ደንብ JHG-RA፣ ወንበዴዎች፣ የውንብድና ተግባር፣ ወይም ሌላ ተመሳሳይ የጥፋት ወይም ህገወጥ የቡድን ስነምግባር መከላከል
ደንብ JNA-RB፣ ከተማሪ የገንዘብ ክፍያ /ፋይናንስ ግዴታዎችን/ መሰብሰብ
ደንብ JPC-RA፣ ለተማሪዎች የመድሃኒት አሰጣጥ

# የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የፀረ-መድሎአዊነት መግለጫ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) በዘር ሐረግ፣ በጎሣ፣ በቀለም፣ በትውልድ ሐረግ፣ በዜግነት፣ በሃይማኖት፣ በስደት ሁኔታ፣ በጾታ፣ በጾታ መገለጫ፣ በጾታ ማንነት፣በጾታዊ ዝንባሌ፣በቤተሰብ መዋቅር/የወላጅነት ሁኔታ፣ በትዳር ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። ዕድሜ፣ ችሎታ (የግንዛቤ፣ ማህበራዊ/ስሜታዊ እና አካላዊ)፣ ድህነት እና ማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ ደረጃ፣ ቋንቋ፣ ወይም ሌላ በህግ ወይም በህገ-መንግሥት ጥበቃ የተደረገላቸው ወይም ትስስር ያላቸው ባህሪያት ላይ የሚደረግ ማናቸውንም ሕገወጥ አድልዎ ይከለክላል። መድሎ ወይም አድሎአዊነት፤ ሕብረተሰባችን ለረዥም ጊዜ እኩልነት፣ ፍትሕ፣ አብሮነት፣ ሁሉን አቀፍነትን፣ ለመፍጠርና ለማሳደግ/ለመንከባከብ ሲደረግ የቆየ ጥረትን ይሸረሽራል/ያበላሻል። ቦርዱ ጥላቻን የሚያራምዱ ቋንቋን እና/ወይም ምስሎችን እንዲሁም ምልክቶችን መጠቀምን ይከለክላል፥ በተለይም በትምህርት ቤት ወይም በዲስትሪክት ሥራ ወይም እንቅስቃሴ ላይ ከፍተኛ ማደናቀፍ ሊያስከትል የሚችል ድርጊት-እንቅስቃሴ የተከለከለ ነው። የበለጠ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ "Montgomery County Board of Education Policy ACA" ይመልከቱ፡- ከአድሎአዊነት ነጻ የሆነ ፍትሃዊነት፥ ሚዛናዊነት፥ እና የዳበረ ባህል "Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency"። ይህ መመርያ እያንዳንዱ ተማሪ ትኩረት የሚሻ መሆኑ(ኗ)ን እና በተለይም የትምህርት ውጤቶች በምንም አይነት በግለሰብ ትክክለኛ ወይም ይሆናል ተብሎ በሚገመት ግላዊ ባህርያት የሚተነበይ እንደማይሆን የቦርዱን እምነት ያረጋግጣል። ፖሊሲው በተጨማሪም ፍትህ/እኩልነትን/ሚዛናዊነትን የሚያዛቡ ነገሮችን ለይቶ በማወቅ በቅድሚያ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎችን፥ የተዛባ ስውር አመለካከትን፣ ጭፍን/መሠረተ-ቢስ ልዩነት ማድረግን፣ በተቋማት የሚፈጸሙ መዋቅራዊ መሰናክሎችን፣ በትምህርት እና በሥራ ላይ እኩልነት እንዳይኖር ተፅእኖ የሚያደርጉ አሠራሮችን የሚገታ/የሚፃረር መሆኑን ያስገነዝባል። MCPS ለወንድ/ሴት ልጅ ስካውት እና ለሌሎች የወጣት ቡድኖች እኩል ተደራሽነት ይሰጣል።**

| MCPS ተማሪዎች ላይ አድልዎ ሲፈጸም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* | MCPS ሰራተኛ ላይ መድሎዎ ሲፈፀም ጥያቄ ወይም ቅሬታ ለማቅረብ* |
|---|---|
| Director of Student Welfare and Compliance<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>SWC@mcpsmd.org | Human Resource Compliance Officer<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| በ1973 የተሃድሶ ህግ ሰክሽን 504 መሠረት ለተማሪ የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ | በአካል ጉዳተኛ አሜሪካውያን ህግ መሠረት ለሰራተኞች የአኮሞዴሽን/መገልገያ ጥያቄ |
| Section 504 Coordinator<br>Office of School Support and Well-being<br>Office of Well-being, Learning and Achievement<br>850 Hungerford Drive, Room 257, Rockville, MD 20850<br>240-740-5630<br>504@mcpsmd.org | ADA Compliance Coordinator<br>Office of Human Resources and Development<br>Department of Compliance and Investigations<br>45 West Gude Drive, Suite 2500, Rockville, MD 20850<br>240-740-2888<br>DCI@mcpsmd.org |
| "Title IX" ድንጋጌ መሠረት፥ ስለ ጾታዊ መድሎአዊነት በተማሪዎች ወይም በሠራተኞች* ላይ ስለሚፈጸምባቸው ጾታዊ ጥቃቶች ጭምር ለሚቀርቡ ጥያቄዎች ወይም ቅሬታዎች | |
| Title IX Coordinator<br>Office of District Operations<br>Student Welfare and Compliance<br>850 Hungerford Drive, Room 55, Rockville, MD 20850<br>240-740-3215<br>TitleIX@mcpsmd.org | |

**ስለ መድሎአዊነት ቅሬታ/አቤቱታ ከዚህ ቀጥሎ ለተዘረዘሩት ሌሎች ኤጀንሲዎችም ማቅረብ ይቻላል፡- U.S. Equal Employment Opportunity Commission (EEOC), Baltimore Field Office, GH Fallon Federal Building, 31 Hopkins Plaza, Suite 1432, Baltimore, MD 21201, 1-800-669-4000, 1-800-669-6820 (TTY); Maryland Commission on Civil Rights (MCCR), William Donald Schaefer Tower, 6 Saint Paul Street, Suite 900, Baltimore, MD 21202, 410-767-8600, 1-800-637-6247, mccr@maryland.gov; or U.S. Department of Education, Office for Civil Rights (OCR), The Wanamaker Building, 100 Penn Square East, Suite 515, Philadelphia, PA 19107, 1-800-421-3481, 1-800-877-8339 (TDD), OCR@ed.gov, or www2.ed.gov/about/offices/list/ocr/complaintintro.html.

**ይህ ማስታወቂያ ከተሻሻለው የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ህግ ጋር የተሳለጠ ነው።

ይህንን ሠነድ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ በተጨማሪ በአማራጭ ቅርጸት ለማግኘት ከተጠየቀ፥ በ "Americans with Disabilities Act" ድንጋጌ መሠረት፣ MCPS Office of Communications በስልክ ቁጥር፡- 240-740-2837፣ 1-800-735-2258 (Maryland Relay)፣ ወይም PIO@mcpsmd.orgበመጠየቅ ማግኘት ይቻላል። የምልክት ቋንቋ ወይም ንግግር ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ግለሰቦች የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ የትርጉም አገልግሎት ጽ/ቤት በዚህ ኤሜይል ወይም ስልክ መጠየቅ ይችላሉ። MCPS Office of Interpreting Services at 240-740-1800, 301-637-2958 (VP) mcpsinterpretingservices@mcpsmd.org, or MCPSInterpretingServices@mcpsmd.org

Maryland's Largest School District

**MONTGOMERY COUNTY PUBLIC SCHOOLS**

ህትመት፡- የዲስትሪክት አቀፍ አገልግሎቶች እና ድጋፎች ጽህፈት ቤት የቁሳቁስ አስተዳደር መምሪያ

0840.23ct • Editorial, Graphics & Publishing Services • 8/23 • 22,686